
እውነትን
ለሚሹ ወገኖች
አዘጋጅና አቅራቢ
ሙሐመድ
(የሰላም ፅኑ)

ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ይህንን መፅሀፍ እንዳዘጋጅ ዕድሜና ጤና ለለገሰኝ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ክብር ምስጋና ለእርሱ የተገባ ይሁን,በመቀጠልም ይህን መፅሀፍ እንዳዘጋጅ የሐሣብ,የሞራልና የማቴሪያል ድጋፍ ላደረጉልኝ ኡስታዘቼና ሙስሊም ወንድሞቼ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ለዚህ መፅሀፍ እንደ ዋነኛ ምንጭ የሸኽ አሕመድ ዲዳትና የተወዳጁ ኡስታዛችን አቡ ሐይደር መፅሐፍቶች በመጠቀሜ,አላህ ከይር ጀዛቸውን ይክፈላቸው።

መታሰቢያነቱ

ዲነል ኢስላምን ለማገልገል እውቀታቸውን,ጊዜአቸውንና ንብረታቸውን መስዋእት ለሚያደርጉ,እውነቱን ከውሸት በመለየት ትክክለኛውን የኢስላም ጎዳና ለሚከተሉና,ይህንን መፅሀፍ አንብበው ካሉበት ጨለማ ወደ ብርሃናዊው የኢስላም ጎዳና ለሚመለሱ ሁሉ ይሁን።

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

መግቢያ.....
ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?.....
የሚያመልከው አምላክ ነበረው.....
የተከበረ የአላህ መልእክተኛ ነው.....
የተከበረ የአላህ ነቢይ ነው.....
የተከበረ የአላህ "ባሪያ" ነው.....
የተከበረ "ሰው" ነው.....
የሚጸልይለት አምላክ ነበረው.....
የአምላክነት ባህሪ የለውም.....
አልተሰቀለም አልሞተም.....
ምጥን ምላሽ ለክርስትያን ወገኖች.....
ያልተፈፀሙ ትንቢቶች.....
እውን ኢየሱስ ስድብን አስተምራልን?.....
ኢየሱስ ብቸኛው የእግዚአብሄር ልጅ ነውን?.....
መፅሀፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ነውን?.....
በውስጡ ያቀፋቸው ግጭቶች.....
አእምሮ ሊቀበላቸው የማይችሉ ፅሁፎች.....
እውነተኛው አምላክ አላህ ወይስ እግዚአብሄር?.....
የአምልኮ ስግደት ለአንድ ፈጣሪ ብቻ.....
የስላሴ አስተምህሮት በቅዱስ ቁርአንና በመፅሀፍ ቅዱስ.....
የእምነት ነፃነት በቅዱስ ቁርአንና በመፅሀፍ ቅዱስ.....
የነብያት ክብር በቅዱስ ቁርአንና በመፅሀፍ ቅዱስ.....
የእግዚአብሄር ባህሪ በመፅሀፍ ቅዱስ.....
የሴቶች መብት በመፅሀፍ ቅዱስ.....
ግድያ በመፅሀፍ ቅዱስ.....
ስለ ነብዩ ሙሐመድየተነገረ(ሰ•ዐ•ወ) ነብይነት የተነገረ ትንቢት.....
ከቁርአን.....
ከመፅሀፍ ቅዱስ.....
ጳውሎስ ማነው?.....
ጥያቄ ለክርስትያን ወገኖች.....
ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት በመፅሀፍ ቅዱስ.....

መግቢያ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው።
ክብር ምስጋና ለአለማቱ ጌታ ለእውነተኛው አምላካችን ለአላህ የተገባ ይሁን,ሰላምና ሰላት የሰው ዘር ታላቅ መሪ ለሆኑት ለነብዩ ሙሐመድ(ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም),ለመላው የአላህ መልእክተኞች,የሐቅንም መንገድ በተከተሉት ሁሉ ላይ ይሁን።

ይህን መፅሀፍ እንዳዘጋጅ ያነሳሳኝ ዋናው ምክንያት,በአሁኑ ሰአት የአክፍሮት ኃይላት ሙስሊሙን ማህበረሰብ ካለበት ብርሃናዊው የኢስላም ጎዳና አስወጥተው ጨለማ ውስጥ ለመክተት የማይፈነቅሉት ድንጋይ,የማይቆፍሩት ጉድጓድ የለም።

ለሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ እንዲሁም አላህ እኔን ሰበብ አድርጎ ሂዳያ ለሚያገኙ ወገኖች ትንሽ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው።

የነሱ ልፋትና ጥሪ ወዴት እንደሆነ እውነተኛው አምላካችን አላህ በተከበረው ቁርአኑ አስቀድሞ ስለነገረን ለኛ ለሙስሊሞች የተሸሸገ ነገር አይደለም።

ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ወደ እምነታቸው ምን እያሉ እንደሚጣሩ,እውነተኛው አምላካችን አላህ በተከበረው ቁርአኑ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

«ገነትንም አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን የኾነ ሰው እንጂ ሌላ አይገባትም» አሉ። ይህቺ (ከንቱ) ምኞታቸው ናት። «እውነተኞች እንደኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ» በላቸው።"(2:111)

በሌላ የቁርአን አንቀፅ አምላካችን አላህ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

«አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን ኹኑ፤ (ቅኑን መንገድ) ትመራላችሁና» አሉም። «አይደለም የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲኾን እንከተላለን፤ ከአጋሪዎችም አልነበረም» በላቸው።"(2:135)

እውነተኛው አምላካችን አላህ በዚህ የቁርአን አንቀፅ,የአባታችን የኢብራሂም ሃይማኖት እንድንከተል አዘዘን።አባታችን ኢብራሂም(ዐለይሂ ሰላም) ሙስሊም እንደነበር በሌላ የቁርአን አንቀፅ በግልፅ ነግሮናል።

ኢብራሒም ይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም ግን ወደ ቀጥተኛዉ ሃይማኖት የተዘነበለ ሙስሊም ነበረ፤ ከአጋሪዎችም አልነበረም።"(3:67)

ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ጥሪያቸው ወደ ጥመት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።
የእነሱ ጥሪ ወደ ከንቱ(ጥመት) እንደሆነ እውነተኛው አምላካችን አላህ በተከበረው ቁርአኑ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

የከሐዲዎችም ጥሪ በከንቱ እንጂ አይደለም"(13:14)

እውነተኛው አምላካችን ኣላህ,አይሁዶችና ክርስትያኖች በዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) ጉዳይ ላይ ድምበር ዘለው የተሳሳተ እምነትና አመለካከት እንዳላቸው በቅዱስ ቃሉ ላይ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ፤ የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ፣ የአላህ መልክተኛ፣ ወደ መርየም የጣላት (የሁን) ቃሉም ከርሱ የሆነ መንፈስም ብቻ ነው፤ በአላህና በመልክተኞቹም እመኑ (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉም፤ ተከልከሉ ለናንተ የተሻለ ይሆናልና፤ አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የርሱ ነው። መመኪያም በአላህ በቃ"(4:171)

አይሁዶች በተከበረው የአላህ መልእክተኛ በዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) ወሰንን አልፈው,አላህ የሰጠውን ክብርና ደረጃ ወደ ጎን በመተው,ዲቃላና ሐሰተኛ ነብይ ይሉታል።

ክርስትያኖች ደግሞ አምላካችን አላህ ለዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የሰጠውን ክብር ትተው,አምላክና ጌታ ብለው ይጠሩታል።

ለዚህ ለተሳሳተው እምነትና አመለካከት በቂ ህክምና ሊሰጥ የሚችል ማስረጃ ያለው የኢየሱስ ማንነት ከመፅሀፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን እንመልከት።

ታዲያ ይሄን መፅሀፍ ስፅፍ ሰው ነኝና,ከብረት ዝገት እንደማይጠፋው ሁሉ ከሰው ልጅም ስህተት አይጠፋም,ይሄን መፅሀፍ እምታነቡ ሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ እንዲሁም ክርስትያን ወገኖች ስህተት ነው እምትሉትን ነገር በዚህ የፌስቡክ አድራሻዬ "የሰላም ልኡክ" እንድትጠቁሙኝ በትህትና እጠይቃለሁኝ።

ክፍል አንድ: ኢየሱስ ክርስቶስ ማነው?

ኢየሱስ ክርስቶስ በመፅሀፍ ቅዱስ በማያሻማና በማያጠራጥር አገላለፅ "እኔ ኢየሱስ አምላክ ነኝ አምልኩኝ ተገዙኝ ወይም ደግሞ እኔ ኢየሱስ ፈጣሪ ነኝ" ብሎ የተናገረበት አንድ ጥቅስ የለም።

መፅሀፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርአን በኢየሱስ ማንነት ዙሪያ ላይ
___ ኢየሱስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው በግልፅ ይናገራሉ።
___ ኢየሱስ የተከበረ ባሪያ,የተከበረ መልእክተኛ,የተከበረ ነብይ,የተከበረ ሰው እንደነበር ያስተምራሉ።
___ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ብሎ እንዳልተሰቀለና እንዳልሞተ ፍንትው አድርገው ያሳያሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው ብዙ መፅሀፍ ቅዱሳዊና ቅዱስ ቁርአናዊ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል።

ለናሙና ያክል, ኢየሱስ ክርስቶስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው ከመፅሀፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ማስረጃዎችን እያጣቀስን እንመልከት:

ከቅዱስ ቁርአን:

• ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) እውነተኛውን አምላክ አላህን ሲያመልክ እንደነበር,አላህን በብቸኝነት ማምለክ እውነተኛውና ቀጥተኛው መንገድ ነው ብሎ እንዳስተማረ ቅዱስ ቁርአናችን በግልፅ ይናገራል።

ለምሳሌ ያክል ማስረጃዎችን ብንመለከት:

1• «አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው፤ ስለዚህ ተገዙት፤ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው» (አላቸው)።"(3:51)

2• (ዒሳ አለ) «አላህም ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።»"(19:36)

3• «አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው።»"(43:64)

ከመፅሀፍ ቅዱስ

መፅሀፍ ቅዱስም ኢየሱስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው በግልፅ ይናገራል።
ለምሳሌ ያክል ማስረጃዎችን ብንመለከት

1• የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ማነው?

"የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።”
(2ኛ ቆሮንጦስ 1:3)

"ለዘላለም የተባረከ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዳልዋሽ ያውቃል።”
(2ኛ ቆሮንጦስ 11:31)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።”(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:3)

የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ”(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:17)

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ”(1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:3-5)

ከላይ ያየናቸው የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች,ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እንደነበረው "የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት" በማለት በግልፅ ያስረዳሉ።

የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ማነው?
እንደ ክርስትያኖች እምነት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,ለአምላክ ሌላ አምላክ እንዴት ይኖረዋል?
ለአምላክ ሌላ አምላክ ካለው,አምላክ ስንት ነው?

2• ኢየሱስን የላከ እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ ማነው?

"እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።"(የዮሀንስ ወንጌል 17:3)

ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ በግልፅ እንደሚናገረው,ኢየሱስን የላከ እውነተኛና ብቸኛ አምላክ እንዳለ ነው።

ኢየሱስን የላከ እውነተኛውና ብቸኛው አምላክ ማነው?

3•ለኢየሱስ ሁሉን ያስገዛለት ማነው?

"ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።"(1ኛ ቆሮንጦስ 15:28)

በዚህ ጥቅስ መሰረት,በስተመጨረሻ ኢየሱስ ሁሉን ላስገዛለት ተገዢ ባሪያ እንደሚሆን በግልፅ ያስረዳል። ለኢየሱስ ሁሉን ያስገዛለት,በስተመጨረሻም ኢየሱስ ለእርሱ ተገዢ እሚሆንለት አካል ማነው?

ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,አምላክ ገዢ ነው ወይስ ተገዢ?
አምላክ ለማን ነው ተገዢ የሚሆነው?

4•የኢየሱስ ኣምላክ ማነው?

"ኢየሱስም፦ ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።"(የዮሀንስ ወንጌል 20:17)

ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ "ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ" ብሎ ሲናገር:

አንደኛው ነጥብ:ኢየሱስ ሲናገር ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ ብሎ ተናገረ።
እንደ ክርስትያኖች እምነት ኢየሱስ አምላክ ከሆነ,የአምላክ ወንድሞች እነማን ናቸው?
አምላክ ተጋሪ የሌለው አንድና ብቸኛ ነው።

ሁለተኛው ነጥብ: ኢየሱስ አምላክ እንዳለው "ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ" በማለት በግልፅ ተናግሯል።
አምላኩ ማነው? አምላኬ እያለ እሚጠራው ማንን ነው?

5• ኢየሱስ,አምላኬ አምላኬ እሚለው ማንን ነው?

"በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም

አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው።”(የማርቆስ ወንጌል 15:34)

"በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፦ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።”(የማቴዎስ ወንጌል 27:46)

ኢየሱስ እራሱ አምላክ ከሆነ,ማንን ነው አምላክ አምላኬ ስለምን ተውከኝ እያለ እሚጠራው?

6•ኢየሱስ ቸር አይደለምን?

"ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።”(የማርቆስ ወንጌል 10:18)

"ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።”(የሉቃስ ወንጌል 18:19)

ኢየሱስ ቸር አለመሆኑን በራሱ አንደበት በግልፅ ከተናገረ,ቸር ያልሆነ አካል እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል?

ኢየሱስ ቸር ካልሆነ,እግዚአብሄር ቸር ከሆነ,ቸር የሆነው እግዚአብሄር,ቸር ያልሆነው ኢየሱስ እንዴት ሊሆን ይችላል?

7• ኢየሱስ ምንን አስተማረ?

"ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው፦ ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥”(የማርቆስ ወንጌል 12:29)

ኢየሱስ አምላክ እንዳለው "ጌታ አምላካችን" በማለት በግልፅ አስተምሯል።
ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለምን ግልፅ በሆነ ቋንቋ "እኔ ነኝ አምላካችሁ" አላለም?

8• ኢየሱስን ጌታ የሚል አይድንም።

"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።”(የማቴዎስ ወንጌል 7:21)

ኢየሱስ ጌታ ስላልሆነ,ጌታ ያልሆነን አካል ጌታ ብለህ ማመንና ጌታ ብለህ መጥራት እንደማያድን በግልፅ እየተናገረ ነው።

ኢየሱስ ጌታ አለመሆኑ በግልፅ ከተናገረ,ጌታ ያልሆነን አካል ጌታ እያሉ በመጥራት የአምላክን ደረጃ መስጠት ለምን አስፈለገ?

ኢየሱስ እሚያመልከው አምላክ እንደነበረው ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ በዚህ መልኩ ካየን,አሁን ደግሞ ኢየሱስ የተከበረ "መልእክተኛ መሆኑን" ቅዱስ ቁርአናዊና መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እያጣቀስን እንመልከት።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተከበረ "መልእክተኛ"

ቅዱስ ቁርአን ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ መልእክተኛ እንደሆነ በግልፅ ያስተምራል።
ለናሙና ያክል ቅዱስ ቁርአናዊ ማስረጃዎችን ብንመለከት:

1• "ወደ እስራኤልም ልጆች መልክተኛ ያደርገዋል።"(3:49)

2• "የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የኾነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም።"(5:75)

3• «እኛ የአላህን መልክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲሕ ዒሳን ገደልን» በማለታቸውም (ረገምናቸው)። አልገደሉትም አልሰቀሉትምም።"(4:157)

4• "የመርየም ልጅ ዒሳም፦ «የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በኾነው የማበስር ስኾን ወደእናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ»"(61:6)

5• "እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ። በአላህም ላይ እውነትን እንጅ አትናገሩ። የመርየም ልጅ አልመሲሕ ዒሳ የአላህ መልክተኛ ወደ መርየም የጣላት «የኹን» ቃሉም ከእርሱ የኾነ መንፈስም ብቻ ነው።"(4:171)

ከነዚህ ቅዱስ ቁርአናዊ ጥቅሶች የምንወስደው ትምህርት ቢኖር

አንደኛ: ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን።
ሁለተኛ:ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተላከበት ማህበረሰብ ወደ እስራኤል ልጆች እንደነበር።

መፅሀፍ ቅዱስ,ኢየሱስ የተከበረ "መልእክተኛ" እንደሆነ በግልፅ ያስተምራል።

ኢየሱስ የተከበረ "መልእክተኛ" ለመሆኑ ለናሙና ያክል "23" የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች እንመልከት:

1• "የምትሰሙትም ቃል "የላከኝ" የኣብ ነው እንጂ የኔ ኣይደለም"(የዬሐንስ ወንጌል 14:24)

2• "እኔ ከራሴ ኣንዳች ላደርግ ኣይቻለኝም እንደሰማሁ እፈርዳሎ ፍርዴም ቅን ነው "የላከኝን" ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን ኣልሻምና"(የዬሐንስ ወንጌል 5:30)

3• "ቃሌን የሚሰማ "የላከኝም" የሚያምን የዘላለም ሂወት ኣለው"(የዬሐንስ ወንጌል 5:24)

4• "ኢየሱስም ጮኽ እንዲህም ኣለ በኔ የሚያምን "በላከኝ" ማመኑ ነው እንጂ በኔ ኣይደለም"(የዬሐንስ ወንጌል 12:44)

5• "እኔ ከራሴ ኣልተናገርሁምና ነገር ግን "የላከኝ" ኣብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ"(

የዬሐንስ ወንጌል 12:49)

6• "የላከኝ" እውነተኛ ነው"(የዬሐንስ ወንጌል 8:26)

7• "የላከኝም" ኣብ ሰለኔ ይመሰክራል"(የዬሐንስ ወንጌል 8:18)

8• "ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም ኣላቸው ትምህርቴስ "ከላከኝ" ነው እንጂ ከኔ ኣይደለም"(የዬሐንስ 7:16)

9• "እኔም በራሴ ኣልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት "የላከኝ" እውነተኛ ነው"(የዬሐንስ ወንጌል 7:28)

10• "እኔንም የጣለ "የላከኝም" ይጥላል"(ሉቃስ ወንጌል 10:16)

11• "ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር "ኣልተላክሁም" ኣለ"(ማቴዎስ 15:34)

12• "ኣንተም "እንደላክኸኝ" ኣመኑ"(የዬሐንስ ወንጌል 17:8)

13•"ይህ የማደርገው ስራ ኣብ "እንደላከኝ" ስለኔ ይመሰክራልና"(የዬሐንስ ወንጌል 5:36)

14•"የላከኝ ኣብም እርሱ ስለኔ መስክሮዋል"(የዬሐንስ ወንጌል 5:37)

15• "እኔ ከእግዚኣብሄር ወጥቼ መጥቻለሁና እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ ኣልመጣሁም"(የዬሐንስ ወንጌል 8:42)

16• "ባሪያ ከጌታው ኣይበልጥም መልእክተኛም ከላከው ኣይበልጥም"
(የዬሐንስ ወንጌል 13:16)

17• "ኣብ እንደላከኝ እኔ ደግሞ "(የዬሐንስ ወንጌል 20:21)

18• "እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።”(የማቴዎስ ወንጌል 10:40)

19• "የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን እንጂ እኔን አይቀበልም አላቸው።”(የማርቆስ ወንጌል 9:37)

20• "ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ስለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ።”(የዮሀንስ ወንጌል 11:42)

21• "አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ”(የዮሀንስ ወንጌል 17:20-21

22• "ጻድቅ አባት ሆይ፥ ዓለም አላወቀህም፥ እኔ ግን አወቅሁህ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ አወቁ” (የዮሀንስ ወንጌል 17:25)

23• "ኢየሱስም፦ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ።"(የዮሀንስ ወንጌል 7:33)

ዒሳ(ኢየሱስ) ዐለይሂ ሰላም የተከበረ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን በዚህ መልኩ ካየን,አሁን ደግሞ ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ "ነብይ" እንደሆነ ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን እያጣቀስን እንመልከት።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተከበረ "ነቢይ"

ከቅዱስ ቁርአን:

እውነተኛው አምላካችን አላህ,ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ "ነቢይ" እንደሆነ በግልፅ ነግሮናል።
ለዚህ ቁርአናዊ ማስረጃው:

(ሕፃኑም) አለ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድረጎኛል።"(19:30)

ከመፅሀፍ ቅዱስ:

መፅሀፍ ቅዱስ ኢየሱስ የተከበረ "ነቢይ" እንደነበር በግልፅ ያስተምራል።

ኢየሱስ ነቢይ እንደነበር "11" መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን ብንመለከት

1•"ኢየሱስም ነቢይ ከገዛ ኣገሩና ከገዛ ዘመዶቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር ኣይቀርም ኣላቸው"(ማርቆስ 6:4)

2• "ኢየሱስ ግን ነቢይ ከገዛ ኣገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር ኣይቀርም ኣላቸው"(ማቴዎስ 13:57)

3• "ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስላዩት"(ማቴዎስ 14:5)

4• "ሕዝቡም ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢዩሱስ ነው ኣሉ"(ማቴዎስ 21:11)

5• "ሊይዙትም ሲፈልጉት ሳሉ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስላዩት ፈሩአቸው"(ማቴዎስ 21:46)

6• "ታላቅ ነቢይ በኛ መካከል ተነሦቶኣል"(ሉቃስ 7:16)

7• "በእግዚኣብሄርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በስራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየየሱስ"(ሉቃስ 24:19)

8• "ከዚህ የተነሳ ሰዎቹ ኢየሱስ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ይህ በእውነት ወደ ኣለም የሚመጣው ነቢይ ነው ኣሉ"(የዬሐንስ ወንጌል 6:14)

9• "ሴቲቱ ጌታ ሆይ ኣንተ ነቢይ እንደ ሆንህ ኣያለሁ"(የዬሐንስ ወንጌል 4:19)

10• "በመካከላቸው መለያየት ሆነ ከዚህም የተነሳ ዕውሩን ኣንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ ኣሉት እርሱም ነቢይ ነው ኣለ"(የዬሐንስ ወንጌል 9:17)

11• "ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ፦ ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤"(የዮሀንስ ወንጌል 7:40)

ከዚህ በመቀጠል ኢየሱስ የተከበረ የአላህ "ባሪያ" እንደሆነ ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን እያጣቀስን እንመልከት:

ኢየሱስ ክርስቶስ የተከበረ "ባሪያ"

ከቅዱስ ቁርአን:

ቅዱስ ቁርአን ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ "ባሪያ" እንደሆነ በግልፅ አስተምሮናል።
ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ የአላህ "ባሪያ" ለመሆኑ ቁርአናዊ ማስረጃዎች ብንመለከት:

1• "(ሕፃኑም) አለ እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፤ መጽሐፍም ሰጥቶኛል ነቢይም አድረጎኛል።"(19:30)

2• "እርሱ በርሱ ላይ የለገስንለት ለእስራኤል ልጆች ታምር ያደረግነው የሆነ ባሪያ እንጂ ሌላ አይደለም።"(43:59)

3• "አልመሲሕ፣ ለአላህ ባሪያ ከመሆን ፈጽሞ አይጠየፍም፤ ቀራቢዎች የሆኑት መላክትም (አይጠየፉም)፤ እርሱን ከመገዛት የሚጠየፍና የሚኮራም ሰው፣ (አላህ) ሁሉንም ወደ እርሱ በእርግጥ ይሰበስባቸዋል"(4:172)

ከመፅሀፍ ቅዱስ:

ኢየሱስ የተከበረ "ባሪያ" ለመሆኑ "8" መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎችን እንመልከት:

1• "እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ"(ኢሳያስ 42:1)

2• "ባሪያዬም በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያጸድቃል፥ ኃጢአታቸውን ይሰከማል።”(ትንቢተ ኢሳያስ 53:11)

3• "እነሆ፥ ባሪያዬ በማስተዋል ያደርጋል፤ ይከብራል ከፍ ከፍም ይላል፥ እጅግ ታላቅም ይሆናል።"(ትንቢተ ኢሳያስ 52:13)

4• "እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ"(ማቴዎስ 12:18)

5• "የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው።"(የሐዋርያት ሥራ 3:13)

6• "ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።"(የሐዋርያት ሥራ 3:26)

7• "በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ"(የሐዋርያት ሥራ 4:27)

8• "አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥"(የሐዋሪያት ሥራ 4:29_30)

የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች "ባሪያ" እሚለውን ቃል "ብላቴና" ብለው ቀይረውታል።
የእንግሊዘኛው መፅሀፍ ቅዱስ "my servant"(ባሪያዬ) ብሎ ይገልፀዋል።
ለምሳሌ ብንመለከት

See my servant, the man of my selection, my loved one in whom my soul is well pleased:"(Gospel of mattew 12:18)

እንግሊዘኛው ላይ "my servant(ባሪያዬ) ብሎ የገለፀውን,አማርኛው ላይ "ብላቴናዬ" ብለው ቀይረውታል።
ባሪያን ወደ ብላቴና መቀየር ለምን አስፈለገ?
መፅሀፍ ቅዱስ በየጊዜው እንደሚቀየር ምንም ጥርጥር የለውም።

ኢየሱስ የተከበረ "ባሪያ" ለመሆኑ በዚህ መልኩ ካየን,አሁን ደግሞ ኢየሱስ የተከበረ "ሰው" ለመሆኑ ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ ማስረጃዎችን እያጣቀስን እንመልከት።

ኢየሱስ ክርስቶስ የተከበረ "ሰው"

ከቅዱስ ቁርአን:

አምላካችን አላህ,ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) የተከበረ ሰው ለመሆኑ በቅዱስ ቁርአኑ በተለያዩ መንገዶች ገልፆልናል።

ለምሳሌ

1• "የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከበፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የሆነ መልክተኛ እንጅ ሌላ አይደለም፤ እናቱም በጣም እውነተኛ ናት፤ (ሁለቱም) ምግብን የሚበሉ ነበሩ፤ አንቀጾችን ለነርሱ (ለከሐዲዎች) እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም (ከውነት) እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት"(5:75)

የሰው ልጅ በሂወት ለመኖር ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ነገሮች አንዱ "ምግብ" ነው።

2• "አላህ ዘንድ የዒሳ ምሳሌ፥ እንደ አዳም ብጤ ነዉ፤ ከዐፈር ፈጠረዉ፤ ከዚያም ለርሱ (ሰዉ) ሁን አለዉ፥ ሆነም።"(3:59)

ከመፅሀፍ ቅዱስ:

ኢየሱስ እንደኛ ሰው እንደነበር "21" መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እንመልከት:

1• "ነገር ግን ኣሁን ከእግዚኣብሄር የሰማሁትን እውነት የነገርኃችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁን"(የዬሐንስ ወንጌል 8:40)

2• "የእስራኤል ሰዎች ሆይ ይህን ቃል ስሙ ራሳችሁ እንደምታውቁ የናዝሬቱ እየሱስ እግዚኣብሄር በመካከላችሁ በርሱ በኩል ባደረገው ታኣምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚኣብሄር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር"(የሐዋርያት ስራ 2:22)

3• "የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ስልጣን ሰጠው"(የዬሐንስ ወንጌል 5:27)
"ሕዝቡም አይተው ተደነቁ፥ ለሰውም እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚኣብሔርን አከበሩ"(የማቴዎስ ወንጌል 9:8)

4• "ኣንድ እግዚኣብሄር ኣለና በእግዚኣብሄርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ ኣንድ ኣለ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ እየሱስ ነው"(1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5)

5• "ነገር ግን የእግዚኣብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ "(ወደ ሮሜ ሰዎች 5:15)

6• "ቀን ቀጥሮኣልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው"(የሐዋሪያት ሥራ 17:31)

7• "በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ። ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ አለ።"(የማርቆስ ወንጌል 15:39)

8• "ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ"(የሉቃስ ወንጌል 2:40)

9• "ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።"(የሉቃስ ወንጌል 2:52)

10• "እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው"(የሉቃስ ወንጌል 24:39)

11• "ኢየሱስም። ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አለው።"(የማቴዎስ ወንጌል 8:20)

12• "ኢየሱስም። እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ።"(የማርቆስ ወንጌል 14:62)

13• "እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ"(የሐዋሪያት ሥራ 7:56)

14• "ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፦ የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው"(የሉቃስ ወንጌል 11:27)

15• "እርሱም በሰተኃላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር"(ማርቆስ ወንጌል 4:38)
"እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር።"(የማቴዎስ ወንጌል 8:24)

16• "በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ"(ማርቆስ ወንጌል 11:12)

"አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።"(የማቴዎስ ወንጌል 4:2)

"በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ።"(የማቴዎስ ወንጌል 21:18)

"አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች ምንም አልበላም፥ ከተጨረሱም በኋላ ተራበ።"(የሉቃስ ወንጌል 4:2)

17• "በዚያም የያዕቆብ ጉድጓድ ነበረ። ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጉድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ።"(ዮሀንስ ወንጌል 4:6)

18• "ኢየሱስም እንባውን አፈሰሰ"(ዮሀንስ ወንጌል 11:35)

19• "ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል"(ዮሀንስ ወንጌል 14:15_16)

20• "(እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።"(ሉቃስ 1:31)

21• "ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ፥ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ፥ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ"(ሉቃስ 2:21)

ኢየሱስ ክርስቶስ "የሚፀልይለት አምላክ" ነበረው።

ኢየሱስ ወደ አምላኩ ይጸልይ እንደነበር "12" መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እንመልከት:

1• "ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።" (የማቴዎስ ወንጌል 14:23)

2• "ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር።"(የሉቃስ ወንጌል 5:16)

3• "በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።" (የሉቃስ ወንጌል 6:12)

4• "እርሱም በአንድ ስፍራ ይጸልይ ነበር”(የሉቃስ ወንጌል 11:1)

5• "በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር”(የሉቃስ ወንጌል 22:44)

6• "አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ።”(የዮሀንስ ወንጌል 12:27)

7• "እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት”(ወደ እብራውያን ሰዎች 5:7)

8• "ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ።”(የማቴዎስ ወንጌል 26:42)

9• "ደግሞም ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ።”(የማቴዎስ ወንጌል 26:44)

10• "ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።”(የማርቆስ ወንጌል 1:35)

11• "ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።"(የሉቃስ ወንጌል 22:41_42)

12• "ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በምድርም ወድቆ፥ ይቻልስ ቢሆን ሰዓቲቱ ከእርሱ እንድታልፍ ጸለየና።አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ።"(የማርቆስ ወንጌል 14:35_36)

ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነት ባህሪ የለውም።

ኢየሱስ ክርስቶስ የአምላክነት ባህሪ እንደሌለው "23" መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች እንመልከት:

1• ኣምላክ እንዳለው መፅሃፍ ቅዱስ በግልፅ ይናገራል።

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ”(2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 1:3)

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ”(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:3)

"የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ”(1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1:3)

2•ኣምላክ እንዳለው እራሱ በግልፅ ተናግሮዋል።

"ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ ዓርጋለሁ”(የዮሐንስ ወንጌል 20:17)

"አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው።”(የማርቆስ ወንጌል 15:34)

"እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው”(የማርቆስ ወንጌል 12:29)

3•እየሱስን ጌታ የሚል ኣይድንም።

"በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ ሰማያት የሚገባ አይደለም”(የማቴዎስ ወንጌል 7:21)

4• ቸር እግዚኣብሄር እንጂ እሱ ቸር እንዳልሆነ ተናግሮዋል።

"ኢየሱስም፦ ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም”(የማርቆስ ወንጌል 10:18)

5•ተልኮ የመጣ "መልእክተኛ" እንደሆነ በግልፅ ተናግሮዋል።

"ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ፦ በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም”(የዮሐንስ ወንጌል 12:44)

"ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና።”(የዮሐንስ ወንጌል 8:42)

"ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ”(የማቴዎስ ወንጌል 15:34)

6• "ነቢይ" እንደነበር መፅሃፍ ቅዱስ ይናገራል።

"ኢየሱስም፦ ነቢይ”(የማርቆስ ወንጌል 6:4)

"ኢየሱስ ግን፦ ነቢይ”(የማቴዎስ ወንጌል 13:57)

"በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤” (የሉቃስ ወንጌል 24:19)

7• "ሰው" እንደነበር መፅሃፍ ቅዱስም እየሱስ እራሱም ያፀድቃሉ።

"ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ” (የዮሐንስ ወንጌል 8:40)

"የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ”(የሐዋርያት ሥራ 2:22)

"አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው”(1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5)

8• ወደ እግዚኣብሄር ይፀልይ ነበር።

"በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ” (የሉቃስ ወንጌል 6:12)

አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ”(የዮሐንስ ወንጌል 12:27)

9• ትምህርቱ ከራሱ ኣይደለም።

"ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም”(የዮሐንስ ወንጌል 7:16)

"እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ” (የዮሐንስ ወንጌል 12:49)

"የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም”(የዮሐንስ ወንጌል 14:24)

10• የሩቅን ነገር ኣያውቅም።

"ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም”(የማቴዎስ ወንጌል 24:36)

"ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም”(የማርቆስ ወንጌል 13:32)

"ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ መጣ፥ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም”(የማርቆስ ወንጌል 11:13)

11• ደከመው

"ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ”(የዮሐንስ ወንጌል 4:6)

12• ተጠማ

"ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ። ተጠማሁ አለ” (የዮሐንስ ወንጌል 19:28)

13• ተራበ

"በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ”(የማርቆስ ወንጌል 11:12)

14• ተገረዘ

"ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ፥ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ፥ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ”(የሉቃስ ወንጌል 2:21)

15• ፆታው ወንድ ነው።

"እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትጼዋለሽ”(የሉቃስ ወንጌል 1:31)

16• ለማኝ ነው።

"ብትወዱኝ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምናለሁ”(የዮሐንስ ወንጌል 14:15)

17• ጡት ይጠባ ነበር።

"የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው”(የሉቃስ ወንጌል 11:27)

18• ከራሱ ምንም ሊያደርግ ኣይችልም።

"አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም”(የዮሐንስ ወንጌል 5:19)

"እኔ ከራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና”(የዮሐንስ ወንጌል 5:30)

19• ተኣምር ሲሰራ የነበረው በእግዚኣብሄር ፈቃድ ነው።

"እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ”(የሉቃስ ወንጌል 11:20)

"እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ”(የማቴዎስ ወንጌል 12:28)

"ኢየሱስም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ። አባት ሆይ፥ ስለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ”(የዮሐንስ ወንጌል 11:41)

20• የራሱ የሆነ ስልጣን ኣልነበረውም።

ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።"(የማቴዎስ ወንጌል 28:18)

"የሰው ልጅም ስለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው”(የዮሐንስ ወንጌል 5:27)

21• ኣብ ከርሱ እንደሚበልጥ በግልፅ ተናግሮዋል።

"የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።"(የዮሐንስ ወንጌል 14:28)

"የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል"(የዮሐንስ ወንጌል 10:29)

22• እንደኛ ይተኛ ነበር።

"እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር" (የማቴዎስ ወንጌል 8:24)

"እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅተውም። መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት"(የማርቆስ ወንጌል 4:38)

23• በሰይጣን ተፈትነዋል።

"ከዚያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው"(ማቴዎስ 4:1)

ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም አልሞተም።

ኢየሱስ ክርስቶስ አለመሰቀሉና አለመሞቱ ከመፅሀፍ ቅዱስ እንመልከት:

ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለምም,አልሞተምም።

•የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች "ኢየሱስ ለኛ ኃጢአት ሲል በቀራንዮ መስቀል ላይ ተሰቅሏል,ሞቷል" የሚል የተሳሳተ እምነትና ኣመለካከት ኣላቸው።

• ይህ የተሳሳተ እምነትና ኣመለካከት በእውቀት መነፅር እንየው።

• ኣንደኛው ነጥብ "ኃጢአት ማለት ምን ማለት ነው"?

"ኃጢአት ማለት የፈጣሪን ትእዛዝ በሀሳብም ሆነ በተግባር መቃወም ነው።"

"ፈጣሪ ይሄን ኣድርግ ብሎ ያዘዘህ ነገር ኣለማድረግ,ኣታድርግ ብሎ የከለከለህን ነገር ደግሞ ማድረግ "ኃጢኣት" ተብሎ ይሰኛል።

• ሁለተኛው ነጥብ "ዛፉን አትብሉ ወይም ዛፍ ኣትብላ" የሚለው የፈጣሪ ትእዛዝ ለማን ነበር???

• ለአዳምና ለሄዋን

ነገር ግን በገነት መካከል ካለው ከዛፉ ፍሬ፥ እግዚአብሔር አለ። እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ አትንኩትም"(ኦሪት ዘፍጥረት 3:3)

• ለአዳም ብቻ

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው። ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፤ነገር ግን መልካምንና ክፉንከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና።"(ኦሪት ዘፍጥረት 2:16)

• ሦስተኛው ነጥብ "አዳምና ሄዋን በሰሩት ኃጢአት እኛ እንዴት እንጠየቃለን"?ኃጢአት እንዴት ይወረሳል?

• ኣዳምና ሄዋን በገነት ውስጥ በነበሩበት ሰአት እኛ ኣልነበርንም።

•ዛፉን ኣትብሉ የሚለው የፈጣሪ ትእዛዝ ለነሱ እንጂ ለኛ ኣልነበረም።

•ዛፉን በልተው የፈጣሪን ትእዛዝ ሲጥሱ የኛ እጅ የለበትም።

ኃጢአት ኣይወረስም።

• የውርስ ኃጢአት በመፅሃፍ ቅዱስም ተቀባይነት እንደሌለው እንመልከት:

1• "አባቶች ስለ ልጆች አይገደሉ፥ ልጆችም ስለ አባቶች አይገደሉ፤ ነገር ግን ሁሉ እያንዳንዱ በኃጢአቱ ይገደል።"(ኦሪት ዘዳግም 24:16)

2• "ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች።"(ትንቢተ ህዝቅኤል 18:4)

3• "ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፤ ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፤ የጻድቁ ጽድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል።"(ትንቢተ ህዝቅኤል 18:20)

4• "ነገር ግን ሰው ሁሉ በገዛ በደሉ ይሞታል፤ መራራውን የወይን ፍሬ የሚበላ ሁሉ ጥርሶቹ ይጠርሳሉ"(ትንቢተ ኤርምያስ 31:30)

• አራተኛው ነጥብ "ኢየሱስ ለነሱ ኃጢአት ከሞተ "ሰዎች ለምን ይሞታሉ? ሴቶችስ በምጥ ለምን ይሰቃያሉ?

ለሴቲቱም አለ። በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፤ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል"(ኦሪት ዘፍጥረት 3:16)

ኢየሱስ ክርስቶስ አልተሰቀለም አልሞተም።

• ኢየሱስ ላለመሰቀሉና ላለመሞቱ ሌላው ማስረጃ,በስቅለት ዙሪያ የተፃፉ ፅሁፎች መጋጨታቸው ነው።

1•ኢየሱስ የመጣው ተሰቅሎ እኛን ለማዳን ከሆነ,ላለመሰቀልና ላለመሞት ፀሎት ማድረግ ለምን ኣስፈለገ?

"እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት"(ወደ ዕብራውያን 5:7)

2• ለመሞት ከመጣ,ይህችን ጽዋ ከኔ ውሰድ እያለ መፀለይ ለምን ኣስፈለገው?

"ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።"(የሉቃስ ወንጌል 22:41_42)

3• ኢየሱስ መቼ ተሰቀለ?መቼ ሞተ?መቼ ተነሳ?3 ቀንና 3 ሌሊት ቆጥሮ እሚያስረዳን ክርስትያን ካለ?

"በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና። መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ።እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው። ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም።ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።"(የማቴዎስ ወንጌል 12:38_40)

4• መስቀሉን የተሸከመው ኢየሱስ ወይስ ስምዖን?

• ስምዖን

"ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት"(የማቴዎስ ወንጌል 27:32)

• ኢየሱስ

"ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ"(የዮሀንስ ወንጌል 19:17)

5•የተሰቀለው 3 ሰዓት ላይ ወይስ 6 ሰዓት ኣከባቢ???

- **3 ሰዓት**

"በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ"(የማርቆስ ወንጌል 15:25)

- **6 ሰዓት**

"ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።እነርሱ ግን። አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም። ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።"(የዮሀንስ ወንጌል 19:14_16)

6•የሰጡት የወይን ጠጅ ቀምሶታል ወይስ ኣልተቀበለም?

- **ኣልተቀበለም**

"ከርቤም የተቀላቀለበትን የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም።"(የማርቆስ ወንጌል 15:23)

- **ቀምሶታል**

"በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።"(የማቴዎስ ወንጌል 27:34)

7• ፈልገው ካላገኙት,እሱ ወዳለበት መምጣት ካልቻሉ የት አግኝተው ሰቀሉት?

"ኢየሱስም። ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ።ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ።"(የዮሀንስ ወንጌል 7:34)

ለኢየሱስ ክርስቶስ ለአምላክነት ለሚቀርቡ ጥቅሶች ምጥን ምላሽ

• ለኢየሱስ አምላክነት እንደ ማስረጃ ተደርገው ለሚቀርቡ ጥቅሶች የተሰጠ ምጥን ምላሽ:

1• "እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ”(የዮሀንስ ወንጌል 13:14)

ክርስትያን ወገኖች ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ "እኔ ጌታና መምህር ስሆን" ማለቱ አምላክና ፈጣሪ ለመሆኑ ማስረጃ ነው ይሉናል።

• አንደኛው ነጥብ

ኢየሱስን ጌታ ያደረገው ማነው?

"አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ”(የሐዋሪያት ሥራ 2:36)

በዚህ ጥቅስ መሰረት ኢየሱስን ጌታ ያደረገው "እግዚአብሄር" ነው።

ኢየሱስን ጌታ ያደረገው እግዚአብሄር ከሆነ,ኢየሱስ ጌታ ከመደረጉ በፊት ምን ነበር???

• ሁለተኛው ነጥብ "ጌታ" የሚለው ቃል እንደ መፅሀፍ ቅዱስ አስተምህሮት አምላክና ፈጣሪ የሚል ትርጉም የለውም።

ጌታዬ ተብለው የተጠሩ ብዙ ሰዎች አሉ።

ለምሳሌ:

1• አብርሃም

"የጌታዬ የአብርሃም አምላክ
እግዚአብሔር ሆይ”(ኦሪት ዘፍጥረት 24:12)

"ሣራም በልብዋ እንዲህ ስትል ሳቀች፦ ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል።”(ኦሪት ዘፍጥረት 18:12)

"እርስዋም፦ ጌታዬ ሆይ፥ ጠጣ አለችው ፈጥናም እንስራዋን በእጅዋ አውርዳ አጠጣችው።”(ኦሪት ዘፍጥረት 24:18)

2• ኤልያስ

"አብድዩም በመንገድ ሲሄድ፥ እነሆ፥ ኤልያስ ተገናኘው አብድዩም አወቀው፥ በግምባሩም ተደፍቶ። ጌታዬ ሆይ፥ ኤልያስ አንተ ነህን? አለ።”(1ኛ መፅሀፈ ነገሦት 18:7)

3• ኤልሳዕ

"የከተማይቱም ሰዎች ኤልሳዕን፦ እነሆ፥ ጌታችን እንደምታይ የዚች ከተማ ኑሮ መልካም ነው፤ ውኃው ግን ክፉ ነው፥ ምድሪቱም ፍሬዋን ትጨነግፋለች አሉት።”(2ኛ መፅሀፈ ነገሦት 2:19)

4• ዮሴፍ

"እነርሱም አሉት። ጌታችን ሆይ አይደለም ባሪያዎችህ ስንዴን ሊገዙ መጥተዋል”(ኦሪት ዘፍጥረት 42:10)

"እንዲህም አሉት፦ ጌታዬ ሆይ፥ ቀድሞ እህልን ልንሸምት ወርደን ነበር”(ኦሪት ዘፍጥረት 43:20)

5• ሲሣራ

"ኢያዔልም ሲሣራን ለመገናኘት ወጥታ። ግባ፥ ጌታዬ ሆይ፥ ወደ እኔ ግባ አትፍራ አለችው”(መፅሀፈ መሳፍንት 4:18)

6• ሙሴ

"አሮንም እንዲህ አለ፦ ጌታዬ ሆይ፥ ቍጣህ አይቃጠል ይህ ሕዝብ ክፋትን እንዲወድድ አንተ ታውቃለህ።” (ኦሪት ዘጸአት 32:22)

"አሮንም ሙሴን፦ ጌታዬ ሆይ፥ ስንፍና አድርገናልና፥ በድለንማልና እባክህ፥ ኃጢአት አታድርግብ”(ኦሪት ዘኅልቁ 12:11)

"ከልጅነቱ ጀምሮ የሙሴ አገልጋይ የነበረው የነዌ ልጅ ኢያሱ። ጌታዬ ሙሴ ሆይ፥ ከልክላቸው አለው” (ኦሪት ዘኅልቁ 11:28)

7•ዔሊ

"ሐናም። ጌታዬ ሆይ፥ አይደለም፥ እኔስ ልብዋ ያዘነባት ሴት ነኝ ጠጅና ሌላ የሚያሰክር ነገር አልጠጣሁም፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ነፍሴን አፈሰስሁ”(1ኛ ሳሙኤል 1:15)

8• መልአክ

"ጌዴዎንም። ጌታዬ ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ይህ ነገር ሁሉ ለምን ደረሰብን?”(መፅሀፈ መሳፍንት 6:13)

9• ኢዮአብ

"ኦርዮም ዳዊትን፦ ታቦቱና እስራኤል ይሁዳም በጎጆ ተቀምጠዋል ጌታዬ ኢዮአብና የጌታዬም ባሪያዎች በሰፊ ሜዳ ሰፍረዋል”(2ኛ ሳሙኤል 11:11)

ኢየሱስ ፍጡር እንጂ ፈጣሪ አይደለም።

ኢየሱስ መልእክተኛ እንጂ አምላክ አይደለም።

2• "በጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።"(የዮሀንስ ወንጌል 1:1)

አንደኛው ነጥብ: በመጀመሪያ የነበረው ቃልና በእግዚአብሄር ዘንድ የነበረው ቃል,ምን የሚል ቃል ነው?
ሁለተኛው ነጥብ: ክርስትያን ወገኖች ኢየሱስ ቃል ነው ቢሉ እንኳ,ጥቅሱ የሚለው "ቃልም በእግዚአብሄር ዘንድ ነበረ" እንጂ "ቃልም እግዚአብሄር ነበረ" አይልም።

ሦስተኛው ነጥብ: ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሄር አይደለም።

1•እግዚአብሄር ሰው አይደለም

"እኔ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና፥ በመካከልህም ቅዱሱ ነኝና የቁጣዬን መቅሠፍት አላደርግም፥ ኤፍሬምንም አጠፋ ዘንድ አልመለስም፤ በመዓትም አልመጣም።"(ትንቢተ ሆሴዕ 11:9)

• ኢየሱስ "ሰው" ነው

"ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ" (የዮሐንስ ወንጌል 8:40)

2•እግዚአብሄር አይደክምም

"አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ፥ የምድርም ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ አይደክምም፥ አይታክትም፥ ማስተዋሉም አይመረመርም።"(ትንቢተ ኢሳያስ 40:28)

•ኢየሱስ ደከመው

"ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ"(የዮሐንስ ወንጌል 4:6)

3•እግዚአብሄር አይተኛም

"እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ አይተኛም አያንቀላፋምም"(መዝሙረ ዳዊት 121:4)

• ኢየሱስ ይተኛ ነበር

"እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ አንቅተውም። መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት"(የማርቆስ ወንጌል 4:38)

4•እግዚአብሄር አይፈተንም

"ማንም ሲፈተን፦ በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።"(የያዕቆብ መልእክት 1:13)

• ኢየሱስ በሰይጣን ተፈትኗል

"ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው"(የማቴዎስ ወንጌል 4:1)

3• "ኢየሱስም አለው። አንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ስኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ። አብን አሳየን ትላለህ?"(ዮሀንስ 14:9)

ይህ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ከበርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ጋር ይጋጫል።

1• "አብን ያየ ማንም የለም"(ዮሀንስ ወንጌል 6:46)

2• "የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም"(ዮሀንስ ወንጌል 5:37)

3• "መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም"(ዮሀንስ ወንጌል 1:18)

4• "እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም"(1ኛ ዮሀንስ መልእክት 4:12)

5• "እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም"(1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16)

6• "ደግሞም። ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ።"(ኦሪት ዘጸአት 33:20)

7• "እጄንም ፈቀቅ አደርጋለሁ፥ ጀርባዬንም ታያለህ፤ ፊቴ ግን አይታይም።"(ኦሪት ዘጸአት 33:23)

8• "በጠላት ፊት እንደ ምሥራቅ ነፋስ እበትናቸዋለሁ፥ በጥፋታቸውም ቀን ጀርባዬን እንጂ ፊቴን አላሳያቸውም።"(ትንቢተ ኤርምያስ 18:17)

ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ተነገሩ የተባሉ ትንቢቶች ተፈፅሟልን?

• ክርስትያን ወገኖች ስለ ኢየሱስ የተነገሩ ትንቢቶች ብለው ለሚያቀርቧቸው ጥቅሶች መልስ የሚሹ ጥያቄዎች

1• "ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች፥ ወንድ ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።"(ትንቢተ ኢሳያስ 7:14)

የኛ ጥያቄ:ማርያም ልጇን "አማኑኤል" ብላ መቼ ጠራችው???

አማኑኤል ብላ ለመጥራቷስ ምን ማስረጃ አላችሁ???

2• "ሕፃን ተወልዶልናልና፥ ወንድ ልጅም ተሰጥቶናልና አለቅነትም በጫንቃው ላይ ይሆናል ስሙም ድንቅ መካር፥ ኃያል አምላክ፥ የዘላለም አባት፥ የሰላም አለቃ ተብሎ ይጠራል።"(ትንቢተ ኢሳያስ 9:6)

የኛ ጥያቄ: ኢየሱስ ክርስቶስ

_ድንቅ መካር
_ኃያል አምላክ
_የዘላለም አባት
_የሰላም አለቃ

ተብሎ መቼ ተጠራ???

3• "እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።"(የማቴዎስ ወንጌል 1:23)

የኛ ጥያቄ:
"እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል" የተባለው መቼ ነው???

ማስረጃችሁን ብታሳዩን

4• "በነቢያት። ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ።"(የማቴዎስ ወንጌል 2:23)

የኛ ጥያቄ:
"በነቢያት ናዝራዊ ይባላል" የተባለው የቱ ጋር ነው???

ኢየሱስ በየትኛው ነቢይ ነው ናዝራዊ የተባለው???
ማስረጃችሁን አሳዩን?

ኢየሱስ ክርስቶስ ስድብን አስተምሯልን?

• እውን ኢየሱስ ይሄን አስተምሯልን???

1• "የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ"(የማቴዎስ ወንጌል 17:17)

"እናንተ የማታምን ጠማማ ትውልድ"(የሉቀስ ወንጌል 9:41)

2• "ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል"(የማቴዎስ ወንጌል 12:39)

"ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል"(የማቴዎስ ወንጌል 16:4)

3• "እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች"(የማቴዎስ ወንጌል 23:17)

"እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች"(የማቴዎስ ወንጌል 23:19)

4• "አንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ"(የማርቆስ ወንጌል 9:25)

5• "እናንት ደንቆሮዎች"(የሉቃስ ወንጌል 11:40)

• ደንቆሮ እያለ እሚሳደብ ፍርዱ "የገሀነም እሳት" ከሆነ,የኢየሱስ እጣ ፈንታው ምንድ ነው?

"እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው

ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።"(የማቴዎስ ወንጌል 5:22)

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ብቸኛው ልጅ ነውን?

• ክርስትያን ወገኖች "ኢየሱስ" የእግዚአብሔር አንዱና ብቸኛው ልጁ ነው በማለት እችን ጥቅስ እንደማስረጃ አድርገው ያቀርባሉ።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።"(የዮሀንስ ወንጌል 3:16)

• እንደ መፅሀፍ ቅዱሱ ገለፃ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ብቻ አይደለም።

1• "የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደ ሆኑ አዩ፤ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 6:2)

2• "እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፤"(ኦሪት ዘጸአት 4:23)

3• "ትእዛዙን እናገራለሁ፤ እግዚአብሔር አለኝ። አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ ወለድሁህ።"(መዝሙረ ዳዊት 2:7)

4• "እኔ ግን። አማልክት ናችሁ፥ ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ፤"(መዝሙረ ዳዊት 82:6)

5• "ከዕለታት አንድ ቀን እንዲህ ሆነ፤ የአምላክ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ለመቆም መጡ፥ ሰይጣንም ደግሞ በመካከላቸው መጣ።"(መጽሐፈ ኢዮብ 1:6)

6• "የእግዚአብሔርም ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ፥"(መጽሐፈ ኢዮብ 38:6)

7• "እኔም አባት እሆነዋለሁ፥ እርሱም ልጅ ይሆነኛል፤ ክፉ ነገርም ቢያደርግ፥ ሰው በሚቀጣበት በትርና በሰው ልጆች መቀጫ እገሥጸዋለሁ፤"(2ኛ ሳሙኤል 7:14)

8• "የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና"(የማቴዎስ ወንጌል 5:9)

9• "በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።"(ሮሜ 8:14)

10• "ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመስል እናውቃለን"(1ኛ የዮሀንስ መልእክት 3:2)

11• "በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጐራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ፤"(ወደ ፊሊጲስዮስ 2:15)

"እውን መፅሀፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ነውን"?

መሉውን መፅሀፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ላለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል።
ሙሉውን መፅሀፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ላለመሆኑ አንዱ ማስረጃው,በውስጡ በርካታ ግጭቶች መኖራቸው ነው።

ሙሉውን መፅሀፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ከሆነ,እርሰ በእርሱ ለምን ተጋጨ?
በመፅሀፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ግጭቶች አሉ,ለናሙና ያክል "35" ግጭቶች እንመልከት:

የፈጣሪ ቃል እርስ በርሱ እንዴት ይጋጫል?

1•

"እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ{ኦሪት ዘፍጥረት 6:6}

ሐሰትን ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፥ ይጸጸትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።"{ኦሪት ዘኅልቁ 23:19}

የኛ ጥያቄ:እግዚአብሄር ይፀፀታል ወይስ ኣይፀፀትም?

2•

"ያዕቆብም። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው{ኦሪት ዘፍጥረት 32:30}

"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤{የዮሀንስ ወንጌል 1:18}

የኛ ጥያቄ:እግዚአብሄርን ያየ ኣለ ወይስ የለም?

3•

"የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ አብ ይበልጣል"{የዮሀንስ ወንጌል 14:28}

"እኔና አብ አንድ ነን{የዮሀንስ ወንጌል 10:30}

የኛ ጥያቄ: ኣብና ወልድ 1 ናቸው ወይስ ኣይደሉም?

4•

"ዳዊትም የዚያ የኤፍራታዊው ሰው ልጅ ነበረ ያም ሰው ከቤተ ልሔም ይሁዳ ስሙም እሴይ ነበረ ስምንትም ልጆች ነበሩት”(1ኛ ሳሙኤል 17:12

"እሴይም የበኵር ልጁን ኤልያብን፥ ሁለተኛውንም አሚናዳብን፥ ሦስተኛውንም ሣማን፥ አራተኛውንም ናትናኤልን፥ አምስተኛውንም ራዳይን፥ ስድስተኛውንም አሳምን፥ ሰባተኛውንም ዳዊትን ወለደ”{1ኛ ዜና 2:13-15)

የኛ ጥያቄ: የእሴይ ልጆች 7 ወይስ 8?

5•

"የብንያምም ልጆች ቤላ፥ ቤኬር፥ አስቤል{ኦሪት ዘፍጥረት 46:21)

"የብንያም ልጆች ቤላ፥ ቤኬር፥ ይዲኤል ሦስት ነበሩ{1ኛ ዜና 7:6}

የኛ ጥያቄ: ሦስተኛው የብንያም ልጅ አስቤል ወይስ ይዲኤል?

6•

"ለዳዊትም ወንድ ልጆች በኬብሮን ተወለዱለት በኵሩም ከኢይዝራኤላዊቱ ከአኪናሆም የተወለደው አምኖን ነበረ።
ሁለተኛውም የቀርሜሎሳዊው የናባል ሚስት ከነበረች ከአቢግያ የተወለደው ዶሎሕያ ነበረ።{2ኛ ሳሙኤል 3:2-3}

በኬብሮንም ለዳዊት የተወለዱለት ልጆች እነዚህ ናቸው። በኵሩ አምኖን ከኢይዝራኤላዊቱ ከአኪናሆም፥ ሁለተኛውም ዳንኤል ከቀርሜሎሳዊቱ ከአቢግያ{1ኛ ዜና 3:1}

የኛ ጥያቄ: ሁለተኛው የዳዊት ልጅ ዶሎሕያ ወይስ ዳንኤል?

7•

"ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ(ኦሪት ዘፍጥረት 17:10)

"መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና(ገላትያ 6:15)

የኛ ጥያቄ: መገረዝ ይጠቅማል ወይስ ኣይጠቅምም?

8•

"በእስራኤልም ሰይፍ የሚመዝዙ 800,000 ጽኑዓን ሰዎች ነበሩ”(መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 24:9)

"ከእስራኤልም ሁሉ 1,100,000 ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21:5)

የኛ ጥያቄ:800,000 ወይስ 1,100,000?

9•

"የይሁዳም ሰዎች 500,000 ነበሩ”(መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 24:9)

"ከይሁዳም 470,000 ሰይፍ የሚመዝዙ ሰዎችን አገኘ”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 21:5)

የኛ ጥያቄ:500,000 ወይስ 470,000?

10•

"መንገሥ በጀመረ ጊዜ አካዝያስ የ 22 ዓመት ጕልማሳ ነበረ”(መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 8:26)

"አካዝያስም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ዕድሜው 42 ዓመት ነበረ”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 22:2)

የኛ ጥያቄ:22 ወይስ 42?

11•

"በኢየሩሳሌምም 3 ወር ነገሠ”(መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 24:8)

"በኢየሩሳሌምም 3 ወርና 10 ቀን ነገሠ”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 36:9)

የኛ ጥያቄ:3 ወር ወይስ 3 ወር ከ10 ቀን?

12•

"እርሱም ጦሩን አንሥቶ 800 ያህል በአንድ ጊዜ ገደለ።”(መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 23:8)

"እርሱ ጦሩን አንሥቶ 300 ሰው በአንድ ጊዜ ገደለ።”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 11:11)

የኛ ጥያቄ:800 ወይስ 300?

13•

"ዳዊትም ከእርሱ 1700 ፈረሰኞች”(መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 8:4)

"7000 ፈረሰኞች”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 18:4)

የኛ ጥያቄ: 1700 ወይስ 7000?

14•

"ለሰሎሞንም በ40,000 ጋጥ የሚገቡ የሰረገላ ፈረሶች”(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 4:26)

"ሰሎሞንም ለፈረሶችና ለሰረገሎች 4000 ጋጥ”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 9:25)

የኛ ጥያቄ: 40,000 ወይስ 4000?

15•

"2000ም የባዶስ መስፈሪያ ይይዝ ነበር።”(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 7:26)

"3000ም የባዶስ መሥፈሪያ ይይዝ ነበር።”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 4:5)

የኛ ጥያቄ: 2000 ወይስ 3000?

16•

"የኤራ ልጆች፥ 775”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:5)

"የኤራ ልጆች፥ 652”(መጽሐፈ ነህምያ 7:10)

የኛ ጥያቄ: 775 ወይስ 652?

17•

"የፈሐት ሞዓብ ልጆች፥ 2812”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:6)

"የፈሐት ሞዓብ ልጆች፥ 2818”(መጽሐፈ ነህምያ 7:11)

የኛ ጥያቄ: 2812 ወይስ 2818?

18•

"የዛቱዕ ልጆች፥ 945”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:8)

"የዛቱዕ ልጆች፥ 845”(መጽሐፈ ነህምያ 7:13)

የኛ ጥያቄ: 945 ወይስ 845?

19•

"የቤባይ ልጆች፥ 623”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:11)

"የቤባይ ልጆች፥ 628”(መጽሐፈ ነህምያ 7:16)

የኛ ጥያቄ: 623 ወይስ 628?

20•

"የዓዝጋድ ልጆች፥ 1222”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:12)

"የዓዝጋድ ልጆች፥ 2322”(መጽሐፈ ነህምያ 7:17)

የኛ ጥያቄ: 1222 ወይስ 2322?

21•

"የአዶኒቃም ልጆች፥ 666”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:13)

"የአዶኒቃም ልጆች፥ 667”(መጽሐፈ ነህምያ 7:18)

የኛ ጥያቄ: 666 ወይስ 667?

22•

"የበጉዋይ ልጆች፥ 2056”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:14)

"የበጉዋይ ልጆች፥ 2067”(መጽሐፈ ነህምያ 7:19)

የኛ ጥያቄ: 2056 ወይስ 2067?

23•

"የዓዲን ልጆች፥ 454”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:15)

"የዓዲን ልጆች፥ 655”(መጽሐፈ ነህምያ 7:20)

የኛ ጥያቄ: 454 ወይስ 655?

24•

"የሐሱም ልጆች፥ 223”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:19)

"የሐሱም ልጆች፥ 328”(መጽሐፈ ነህምያ 7:22)

የኛ ጥያቄ: 223 ወይስ 328?

25•

"የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ 223”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:28)

"የቤቴልና የጋይ ሰዎች፥ 123”(መጽሐፈ ነህምያ 7:32)

የኛ ጥያቄ: 223 ወይስ 123?

26•

"200 ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩአቸው”(መጽሐፈ ዕዝራ 2:65)

"245 ወንዶችና ሴቶች መዘምራን ነበሩአቸው”(መጽሐፈ ነህምያ 7:67)

የኛ ጥያቄ: 200 ወይስ 245?

27•

"በመቅሠፍትም የሞተው ሀያ አራት ሺህ ነበረ”(ኦሪት ዘኍልቍ 25:9)

"በአንድ ቀንም ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ አንሴስን”(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 10:8)

የኛ ጥያቄ: 24,000 ወይስ 23,000?

28•

"የሸማያም ልጆች ሐጡስ፥ ይግኣል፥ ባርያሕ፥ ነዓርያ፥ ሻፋጥ ስድስት ነበሩ።"(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ 3:22)

የኛ ጥያቄ: 5 ወይስ 6?

29•

"ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።"(የማቴዎስ ወንጌል 27:32)

"ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት ወጣ።"(የዮሀንስ ወንጌል 19:17)

የኛ ጥያቄ:መስቀሉን ማን ተሸከመው? ስሞዖን ወይስ ኢየሱስ?

30•

"ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።"(የማቴዎስ ወንጌል 27:5)

"ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ"(የሐዋሪያት ሥራ 1:18)

የኛ ጥያቄ: ይሁዳ የሞተው ታንቆ ወይስ በግንባሩ ተደፍቶ አንጀቱ ተዘርግፎ?

31•

"እኔ ስለ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም"(የዮሀንስ ወንጌል 5:31)

"እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው"(የዮሀንስ ወንጌል 8:14)

የኛ ጥያቄ: ምስክርነቱ እውነት ነው ወይስ አይደለም?

32•

"በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ"(የማርቆስ ወንጌል 15:25)

"ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው። እነርሱ ግን። አስወግደው፥ አስወግደው፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። ንጉሣችሁን ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም። ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት። ስለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።"(የዮሀንስ ወንጌል 19:14_16)

የኛ ጥያቄ: ኢየሱስ የተሰቀለው 3 ሰአት ላይ ወይስ 6 ሰአት ላይ?

33•

"እንዲህም ሆነ የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማከረ በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ ሰባተኛው ቀን የባቢሎን ንጉሥ ዮርማሮዴቅ በነገሠ በአንደኛው ዓመት የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪንን ከወህኒ አወጣው"(2ኛ ነገሦት 25:27)

"እንዲህም ሆነ የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ሰባተኛው ዓመት በአሥራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ አምስተኛው ቀን፥ የባቢሎን ንጉሥ ዮርማሮዴክ በነገሠ በአንደኛው ዓመት የይሁዳን ንጉሥ የዮአኪንን ራስ ከፍ ከፍ አደረገ ከወህኒም አወጣው"(ትንቢተ ኤርሚያስ 52:31)

የኛ ጥያቄ: በ 25ኛው ቀን ወይስ በ27ኛው ቀን?

34•

"አሮንም በሖር ተራራ በሞተ ጊዜ ዕድሜው መቶ ሀያ ሦስት ዓመት ነበር።"(ኦሪት ዘኅልቁ 33:39)

የእስራኤልም ልጆች ከብኤሮት ብኔያዕቃን ወደ ሞሴራ ተጓዙ በዚያም አሮን ሞተ"(ኦሪት ዘዳግም 10:6)

የኛ ጥያቄ: አሮን የሞተው በሖር ተራራ ወይስ ሞሴራ?

35•

"በኢየሩሳሌምም ሦስት ዓመት ነገሠ እናቱም መዓካ የተባለች የአቤሴሎም ልጅ ነበረች።"(1ኛ ነገሦት 15:2)

"ሦስት ዓመት በኢየሩሳሌም ነገሠ የእናቱም ስም ሚካያ ነበረ የገብዓ ሰው የኡርኤል ልጅ ነበረች"(2ኛ ዜና 13:2)

የኛ ጥያቄ: የአብያ እናት መዓካ ወይስ ሚካያ?

"እግዚአብሄርን ያየ አለ ወይስ የለም"?

ስለ እግዚአብሄር መታየት መፅሀፍ ቅዱስ እርሰ በእርሱ እሚጣረስ መልእክት ይዟል።

• እግዚአብሄርን ያየ የለም የሚሉ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች

"እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም"(1ኛ የዮሀንስ መልእክት 4:12)

"ደግሞም፦ ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም አለ።"ኦሪት ዘጸአት 33:20)

"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።"(የዮሀንስ ወንጌል 1:18)

"የላከኝ አብም እርሱ ስለ እኔ መስክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም"(የዮሀንስ ወንጌል 5:37)

"አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን አይቶአል።"(የዮሀንስ ወንጌል 6:46)

"እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም"(1ኛ ጢሞቴዎስ 6:16)

• እግዚአብሄርን ያዩ እንዳሉ የሚናገሩ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች

"ሙሴም አሮንም ናዳብም አብዩድም ከእስራኤልም ሰባ ሽማግሌዎች ወጡ
የእስራኤልንም አምላክ አዩ ከእግሩም በታች እንደ ሰማይ መልክ የሚያበራ እንደ ብሩህ ሰንፔር ድንጋይ የሚመስል ወለል ነበረ።እጁንም በእስራኤል አዛውንቶች ላይ አልዘረጋም እነርሱም እግዚአብሔርን አዩ፥ በሉም ጠጡም።"(ኦሪት ዘጸአት 24:9_11)

"ንጉሡ ዖዝያን በሞተበት ዓመት እግዚአብሔርን በረጅምና ከፍ ባለ ዙፋን ላይ ተቀምጦ አየሁት፥ የልብሱም ዘርፍ መቅደሱን ሞልቶት ነበር።"(ትንቢተ ኢሳያስ 6:1)

"ያዕቆብም። እግዚአብሔርን ፊት ለፊት አየሁ፥ ሰውነቴም ድና ቀረች ሲል የዚያን ቦታ ስም ጵኒኤል ብሎ ጠራው።"(ኦሪት ዘፍጥረት 32:30)

"ሚክያስም አለ። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ስማ እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ፥ የሰማይም ሠራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው አየሁ።"(1ኛ ነገስት 22:19)

"ሚክያስም አለ። እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ፥ የሰማይም ሠራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው አየሁ።"(2ኛ ዜና 18:18)

የትኛው ነው ትክክል???

ሙሉውን መፅሀፍ ቅዱስ የአምላክ ቃል ላለመሆኑ ሌላው ማስረጃ,አእምሮ ሊቀበላቸው የማይችሉ ነገሮች በውስጡ አካቶ መያዙ ነው።

1• በጎች በትሮችን በማየት ብቻ ፀነሱ,ከዛም ወለዱ

"በጎቹም በትሮቹን አይተው ከመጎምጀታቸው የተነሣ ፀነሱ በጎቹም ሸመልመሌ መሳይና ዝንጉርጉር ነቊጣም ያለበቱን ወለዱ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 30:39)

2•የወር አበባ ያየች ሴት እርኩስ ነች

"ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች፤ የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።
መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው።መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው።የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።
በመኝታዋም ላይ ወይም በምትቀመጥበት ነገር ላይ ቢሆን ሲነካው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።ማንም ከእርስዋ ጋር ቢተኛ መርገምዋም ቢነካው፥ ሰባት ቀን ርኩስ ነው፤ የሚተኛበትም መኝታ ሁሉ ርኩስ ነው።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 15:19_24)

3•ጋብቻ በግድ

"ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፥ ከእርስዋም ጋር ይኑር።"(ኦሪት ዘዳግም 25:5)

4•ራቁትህንና ባዶ እግርህን እየተንዘላዘልክ መሄድ ምን ተአምር ሆነና ነው?

"እግዚአብሔርም አለ፦ ባሪያዬ ኢሳይያስ በግብጽና በኢትዮጵያ ላይ ሦስት ዓመት ለምልክትና ለተአምራት ሊሆን ራቁቱንና ባዶ እግሩን እንደ ሄደ"(ኦሪት ዘዳግም 20:3)

5• ብልቱን ብትይዝ እጇን ቁረጥ

"ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ፥ የአንደኛውም ሚስት ባልዋን ከሚመታው ሰው እጅ ታድነው ዘንድ ብትቀርብ፥ እጅዋንም ዘርግታ ብልቱን ብትይዝ፥እጅዋን ቊረጥ፥ ዓይንህም አትራራላት።"(ኦሪት ዘዳግም 25:11_12)

6•የሞተን ሰው በድን የነካ ለ 7 ቀን ርኩስ ነው

"የሞተውን ሰው በድን የሚነካ ሰባት ቀን ርኩስ ይሆናል"(ኦሪት ዘኅልቁ 19:11)

7•ወላጆቹን እማይታዘዝ ይገደል

"ማንም ሰው ለአባቱ ቃልና ለእናቱ ቃል የማይታዘዝ ቢቀጡትም የማይሰማቸው እልከኛና ዓመፀኛ ልጅ ቢኖረው፥አባቱና እናቱ ይዘው ወደ ከተማው ሽማግሌዎች ወደሚኖሩበትም ስፍራ በር ያምጡት፤የከተማውንም ሽማግሌዎች። ይህ ልጃችን እልከኛና ዓመፀኛ ነው፥ ለቃላችንም አይታዘዝም ስስታምና ሰካራም ነው ይበሉአቸው።የከተማውም ሰዎች ሁሉ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩት፤ "(ኦሪት ዘዳግም 21:18_21)

8•እውን ፈጣሪ እንዲህ ብሎ አዘዘ?

"ለእንግዳው በወለድ አበድረው፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር በሥራህ ሁሉ ይባርክህ ዘንድ ለወንድምህ በወለድ አታበድር።"(ኦሪት ዘዳግም 23:20)

9•ፈጣሪ አካለ ጎደሎ የሆኑትን ያገላቸዋልን?

"እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው።ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው። ከዘርህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ።ዕውር፥ ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥ ወይም፤ ትርፍ አካል ያለው፥
ወይም እግረ ሰባራ፥ ወይም እጀ ሰባራ፥ወይም ጐባጣ፥ ወይም ድንክ፥ ወይም ዓይነ መጭማጫ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍቻም፥ ወይም ጃንደረባ፥ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ"(ኦሪት ዘሌዋውያን 21:16_20)

10•ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም

"የሰው ልጆችና የእንስሳ እድል ፈንታ አንድ ነው፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ሁሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም።"(መጽሀፈ መክብብ 3:19)

11•ይሄም የፈጣሪ ቃል ነውን?

"ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ።"(2ኛ ጢሞቴዎስ 4:13)

12• ይሄ የፍቅር ደብዳቤም የፈጣሪ ቃል?

"አንቺ ሱላማጢስ ሆይ፥ ተመለሽ፥ ተመለሽ፤ እናይሽ ዘንድ ተመለሽ፥ ተመለሽ። በሱላማጢስ ምን ታያላችሁ? እርስዋ እንደ መሃናይም ዘፈን ናት።አንቺ የመኰንን ልጅ ሆይ፥ እግሮችሽ በጫማ ውስጥ እንዴት ውቦች ናቸው! ዳሌዎችሽስ በአንጥረኛ እጅ እንደ ተሠሩ እንደ ዕንቊዎች ይመስላሉ።እንብርትሽ የወይን ጠጅ እንደማይጐድልበት እንደ ተነጠጠ ጽዋ ነው፤ ሆድሽ እንደ ስንዴ ክምር፥ በአበባም እንደ ታጠረ ነው።ሁለቱ ጡቶችሽ እንደ ሁለቱ መንታ እንደ ሚዳቋ ግለገሎች ናቸው።አንገትሽ እንደ ዝሆን ጥርስ ግንብ ነው፤ ዓይኖችሽ በሐሴቦን ውስጥ በባትረቢ በር አጠገብ እንደ ውኃ ኵሬዎች ናቸው፤ አፍንጫሽ ወደ ደማስቆ አፋዛዥ እንደሚመለከት እንደ ሊባኖስ ግንብ ነው።ራስሽ እንደ ቀርሜሎስ ተራራ በላይሽ ነው፤ የራስሽም ጠጕር እንደ ሐምራዊ ሐር ነው፤ ንጉሡ በሹርባው ታስሮአል።ወዳጄ ሆይ፥ እንዴት የተዋብሽ ነሽ! እንዴትስ ደስ ታሰኛለሽ!ይህ ቁመትሽ የዘንባባ ዛፍ ይመስላል፥ ጡቶችሽም የወይን ዘለላ ይመስላሉ።ወደ ዘንባባው ዛፍ እወጣለሁ ጫፎችዋንም እይዛለሁ አልሁ፤ ጡቶችሽ እንደ ወይን ዘለላ የአፍንጫሽም ሽቱ እንደ እንኮይ ናቸው"(መኃልየ መኃልየ ዘሰሎሞን 7:1_9)

13•እችኛዋስ?

"ቊላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቈረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ"(ኦሪት ዘዳግም 23:1)

"እውነተኛው ኣምላክ ኣላህ ወይስ እግዚኣብሄር"?

እኛ ሙስሊሞች እንደምናምነው,ቁርአናችንም እንደሚያስተምረው እውነተኛው አምላክ ኣላህ ብቻ ነው,ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ብለን እናምናለን።

ክርስትያን ወገኖች ደግሞ በተቃራኒው,እግዚአብሔር እውነተኛው አምላክ ነው ብለው ያምናሉ።

እውነተኛው አምላክ ማን እንደሆነ,ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ እያጣቀስን እንመልከት።

1•እውነተኛው ኣምላክ ድካም ኣይሰማውም

- **ኣላህ በቁርኣኑ**

"ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን። ድካምም ምንም አልነካንም።"(50:38)

- **እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ**

"እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፥ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ፥ በእኔና በእስራኤል ልጆች ዘንድ የዘላለም ምልክት ነው።"(ኦሪት ዘፀኣት 31:17)

2•እውነተኛው ኣምላክ ኣይተኛም ኣያንቀላፋም

•ኣላህ በቁርኣኑ

"አላህ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ማንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም።"(2:255)

• እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ

"አቤቱ፥ ንቃ፤ ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን።"(መዝሙረ ዳዊት 44:23)

3•እውነተኛው ኣምላክ ከኣስካሪ መጠጥ ይከለክላል።

• ኣላህ በቁርኣኑ

"እናንተ ያመናችሁ ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ ቁማርም ጣዖታትም አዝላምም ከሰይጣን ሥራ የኾኑ እርኩስ ብቻ ናቸው። (እርኩስን) ራቁትም ልትድኑ ይከጀላልና።"(5:90)

• እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ

"ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት፤"(መፅሃፈ ምሳሌ 31:6)

4• እውነተኛው ኣምላክ በዝሙት ኣያዝም

• ኣላህ በቁርኣኑ

"ዝሙትንም አትቅረቡ። እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና። መንገድነቱም ከፋ!"(17:32)

• እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ

"እግዚአብሔር መጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሆሴዕን። ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለችና ሂድ፤ ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ አለው።"(ትንቢተ ሆሴእ 1:2)

5•እውነተኛው ኣምላክ ከፍጡራን ኣይከጅልም

• ኣላህ በቁርኣኑ

"እናንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ። አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው።"(35:15)

• **እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ**

"በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።"(ኢሳያስ 7:20)

6• እውነተኛው ኣምላክ ኣንዱ በሰራው ኃጢኣት ሌላኛውን ኃጢኣተኛ ኣያደርግም

• **ኣላህ በቁርኣኑ**

"ተሸካሚም (ነፍስ) የሌላይቱን ኃጢኣት አትሸከምም።"(17:15)

• **እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ**

"ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ፤ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።"(ኦሪት ዘዳግም 23:2)

7• እውነተኛው ኣምላክ በሃይማኖት ኣያስገድድም

• **ኣላህ በቁርኣኑ**

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም።"(2:256)

• **እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ**

"የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ፥ ታናሽ ወይም ታላቅ፥ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን፥ ይገደል"(2ኛ ዜና 15:13)

8• እውነተኛው ኣምላክ በማንም ኣይሸነፍም

• **ኣላህ በቁርኣኑ**

"አላህን ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም። አላህ በጣም ኃያል አሸናፊ ነው።"(22:74)

• **እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ**

"አለውም። ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል፤ ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና።"(ኦሪት ዘፍጥረት 32:28)

9• እውነተኛው አምላክ "ወለድ(አራጣ)ን" አይፈቅድም።

• **ኣላህ በቁርአኑ**

"መሸጥን አላህ ፈቅዷል። አራጣንም እርም አድርጓል።"(2:275)

• **እግዚአብሔር በመፅሀፍ ቅዱስ**

ለእንግዳው በወለድ አበድረው፤ ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ልትወርሳት በምትገባባት ምድር በሥራህ ሁሉ ይባርክህ ዘንድ ለወንድምህ በወለድ አታበድር።"(ኦሪት ዘዳግም 23:20)

10• ሁሉም የሰው ልጅ የተከበረ ነው።

• **ኣላህ በቁርአኑ**

የአደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው በየብስን በባሕርም አስሳፈርናቸው፤ ከመልካሞችም (ሲሳዮች) ሰጠናቸው፤ ከፈጠርናቸውም ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።"(17:70)

• **እግዚአብሄር በመፅሀፍ ቅዱስ**

እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው።ለአሮን እንዲህ ብለህ ንገረው። ከዘርህ በትውልዳቸው ነውር ያለበት ሰው ሁሉ የአምላኩን እንጀራ ያቀርብ ዘንድ አይቅረብ።ዕውር፥ ወይም አንካሳ፥ ወይም አፍንጫ ደፍጣጣ፥ ወይም፤ ትርፍ አካል ያለው፥ወይም እግረ ሰባራ፥ ወይም እጀ ሰባራ፥ወይም ጐባጣ፥ ወይም ድንክ፥ ወይም ዓይነ መጭማጫ፥ ወይም እከካም፥ ወይም ቋቍቻም፥ ወይም ጃንደረባ፥ ነውረኛ ሁሉ አይቅረብ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 21:16_20)

11• እውነተኛው አምላክ "በክት" እንድንበላ አያዝም።

• **ኣላህ በቁርአኑ**

በናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን፣ የእሪያ ሥጋንም"(2:173)

• **እግዚአብሔር በመፅሀፍ ቅዱስ**

አንተ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ሕዝብ ነህና የበከተውን ሁሉ አትብላ፤ ይበላው ዘንድ በአገርህ ደጅ ለተቀመጠ መጻተኛ ትሰጠዋለህ፥ ወይም ለእንግዳ ትሸጠዋለህ።"(ኦሪት ዘዳግም 14:21)

12• እውነተኛው አምላክ "ሁሉን አዋቂ" ነው።

• **ኣላህ በቁርአኑ**

የሩቅ ነገርም መክፈቻዎች እርሱ ዘንድ ናቸው። ከእርሱ በቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባሕር ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ከቅጠልም አንዲትም አትረግፍም የሚያውቃት ቢኾን እንጅ። ከቅንጣትም በመሬት ጨለማዎች ውስጥ የለም ከእርጥብም ከደረቅም አንድም የለም ግልጽ በኾነው መጽሐፍ ውሰጥ (የተመዘገበ) ቢኾን እንጅ። "(6:59)

• እግዚአብሔር በመፅሀፍ ቅዱስ

እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 11:5)

"የአምልኮ ስግደት ለ 1 ፈጣሪ ብቻ"

• ከቅዱስ ቁርአን

1•"ሌሊትና ቀንም፣ ጸሐይና ጨረቃም፣ ከምልክቶቹ ናቸው፤ ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ፤ ለዚያም ለፈጠራቸው አላህ ሰገዱ፤ እርሱን ብቻ የምትግገዙ እንደሆናችሁ፣ (ለሌላ አትስገዱ)"(41:37)

2•"«ስግደቴ፣ መገዛቴም፣ ሕይወቴም፣ ሞቴም ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው» በል።"(6:162)

3•"ስለዚህ ለጌታህ ስገድ።"(108:2)

• ከመፅሀፍ ቅዱስ

1•ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።በላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው፥ ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ።አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም፤"(ኦሪት ዘጸአት 20:3_5)

2•ለአማልክቶቻቸው አትስገድ፥ አታምልካቸውም፤ እንደ ሥራቸውም አትሥራ፤ ነገር ግን ፈጽመህ አፍርሳቸው፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብራቸው"(ኦሪት ዘጸአት 23:24)

3•ስሙ ቀናተኛ የሆነ እግዚአብሔር ቅንዓት ያለው አምላክ ነውና ለሌላ አምላክ አትስገድ።"(ኦሪት ዘጸአት 34:14)

4•በሚጠሉኝ እስከ ሦስተኛና እስከ አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፤ ለሚወድዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውም።"(ኦሪት ዘዳገረም 5:9_10)

"የስላሴ አስተምህሮት በቁርአንም ሆነ በመፅሀፍ ቅዱስ ተቀባይነት የለውም"

እውነተኛው አምላክ አንድ ነው,በአንድነቱ ውስጥ ሁለትነት ወይም ሦስትነት የለበትም።

ቁርአናዊ ማስረጃው

1•አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው፤ ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የለም። (እርሱ) እጅግ በጣም ርኅሩህ አዛኝ ነው።"(2:163)

2•አምላካችሁ በእርግጥ አንድ ነዉ።"(37:4)

3•በል፦ እርሱ አላህ አንድ ነው"(112:1)

4•አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው"(16:22)

መፅሀፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው

1•እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤"(ኦሪት ዘዳግም 6:4)

2•መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም እግዚአብሔር ግን አንድ ነው"(ገላትያ 3:20)

3•አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው"(1ኛ ጢሞቴዎስ 2:5)

4•ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው"(የማርቆስ ወንጌል 12:29)

5•እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ስለ መብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከአንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን።"(1ኛ ቆሮንጦስ 8:4)

6•ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን"(1ኛ ቆሮንጦስ 8:6)

7•አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደ ሆንሁ፥
ከእኔም በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤
እኔ እገድላለሁ፥ አድንማለሁ፤
እኔ እመታለሁ፥ እፈውስማለሁ፤
ከእጄም የሚያድን የለም።"(ኦሪት ዘዳግም 32:39)

በእስልምና አስተምህሮት በሃይማኖት ማስገደድ የለም።

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።"(2:256)

እውነቱም፥ ከጌታችሁ ነው፤ የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ፣ በላቸው"(18:29)

ከነዛ በሃይማኖት ካልተጋደሏችሁ ከአገሮቻችሁም ካላወጧችሁ (ከሐዲዎች) መልካም ብትውሉላቸውና ወደነሱ ብታስተካክሉ አላህ አይከለክላችሁም፤ አላህ ትክክለኞችን ይወዳልና።"(60:8)

በክርስትና አስተምህሮት የእምነት ነፃነት የለም።

"የእናትህ ልጅ ወንድምህ ወይም ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ ወይም በብብትህ ያለች ሚስትህ ወይም እንደ ነፍስህ ያለ ወዳጅህ በስውር። ና፥ ሄደን ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ ወደ አንተ የቀረቡት ከአንተም የራቁት አንተን ከብበውህ ያሉ አሕዛብ ከሚያመልኩአቸው አማልክት፥ አንተም አባቶችህም የማታውቋቸውን ሌሎች አማልክት እናምልክ ብሎ ቢያስትህ፥ እሺ አትበለው አትስማውም፤ ዓይንህም አይራራለት፥ እትማረውም፥ አትሸሽገውም፤ነገር ግን ፈጽመህ ግደለው፤ እርሱን ለመግደል በፊት የአንተ እጅ፥ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ትሁን።"(ኦሪት ዘዳግም 13:6_9)

" አምላክህ እግዚአብሔር ልትኖርባት በሚሰጥህ በአንዲቱ ከተማህ። ክፋተኞች ሰዎች ከእናንተ ዘንድ ወጥተው። ሄደን የማታውቋቸውን ሌሎችን አማልክት እናምልክ ብለው የከተማቸውን ሰዎች አሳቱ ሲሉ ወሬ ብትሰማ፥ትፈልጋለህ፥ ትመረምራለህም፥ ትጠይቃለህም፤ እነሆም፥ እውነት ቢሆን፥ ይህም ክፉ ነገር በመካከልህ እንደ ተደረገ እርግጥ ሆኖ ቢገኝ፥
የዚያችን ከተማ ሰዎች በሰይፍ ስለት ፈጽሞ ትመታቸዋለህ፤ ከተማይቱን፥ በእርስዋም ያለውን ሁሉ፥ እንስሳውንም በሰይፍ ስለት ታጠፋቸዋለህ"(ኦሪት ዘዳግም 13:12_15)

"አምላክህ እግዚአብሔር ከሰጠህ ከአገርህ ደጆች በማንኛይቱም ውስጥ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን ቃል ኪዳኑን በማፍረስ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ክፋት የሠራ ቢገኝ፥ሄዶም ሌሎች አማልክትን ያመለከ፥ እኔ ላላዘዝኋቸው ለፀሐይና ለጨረቃ ለሰማይም ሠራዊት ሁሉ የሰገደ ቢገኝ፥ቢያወሩልህም ብትሰማም፥ ያንን ፈጽመህ መርምር፤ እነሆም፥ እውነት ቢሆን፥ በእስራኤልም መካከል እንዲህ ያለ ርኵሰት እንደ ተሠራ እርግጥ ሆኖ ቢገኝ፥ይህን ክፉ ነገር የሠሩትን ያን ወንድ ወይም ያችን ሴት ወደ በርህ ታመጣቸዋለህ፥ እስኪሞቱም ድረስ በድንጋይ ትወግራቸዋለህ።"(ኦሪት ዘዳግም 17:2_5)

"የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ፥ ታናሽ ወይም ታላቅ፥ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን፥ ይገደል ዘንድ ማሉ።"(2ኛ ዜና 15:13)

"የነብያት ክብር በቅዱስ ቁርኣንና በመፅሃፍ ቅዱስ"

1•

•ሉጥ(ዐለይሂ ሰላም) በቁርኣን

"ሉጥንም ፍርድንና ዕውቀትን ሰጠነው። ከዚያችም መጥፎ ሥራዎችን ትሠራ ከነበረችው ከተማ አዳንነው። እነሱ ክፉ ሰዎች አመጸኞች ነበሩና፡
በችሮታችንም ውስጥ አገባነው። እርሱ ከመልካሞቹ ነውና።(21:74_75)

• ሎጥ በመፅሃፍ ቅዱስ ዝሙት ከ2 ሴት ልጆቹ ፈፀመ

"የሎጥም ሁለቱ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው ፀነሱ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 19:36)

2•

•ኑሕ(ዐለይሂ ሰላም) በቁርኣን

"አላህ አደምን፣ ኑሕንም፣ የኢብራሂምንም ቤተሰብ፣ የዒምራንንም ቤተሰብ በዓለማት ላይ መረጠ።።"(3:33)

• ኖህ በመፅሃፍ ቅዱስ ሰክሮ ራቁቱን ሆነ

"ከወይን ጠጁም ጠጣና ሰከረ፤ በድንኳኑም ውስጥ ዕራቁቱን ሆነ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 9:21)

3•

• ሃሩን(ዐለይሂ ሰላም) በቁርኣን

"ከችሮታችንም ወንድሙን ሃሩንን ነቢይ አድርገን ሰጠነው።"(19:53)

• ኣሮን በመፅሃፍ ቅዱስ ጣኦት ሰሪ ነበር

"አሮንም። በሚስቶቻችሁ በወንዶችና በሴቶች ልጆቻችሁም ጆሮ ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብራችሁ አምጡልኝ አላቸው።ሕዝቡም ሁሉ በጆሮቻቸው ያሉትን የወርቅ ቀለበቶች ሰብረው ወደ አሮን አመጡለት።ከእጃቸውም ተቀብሎ በመቅረጫ ቀረጸው፥ ቀልጦ የተሠራ ጥጃም አደረገው፤ እርሱም። እስራኤል ሆይ፥ እነዚህ ከግብፅ ምድር ያወጡህ አማልክትህ ናቸው አላቸው።"(ኦሪት ዘፀኣት 32:2_4)

4•

• ዳውድ(ዐለይሂ ሰላም) በቁርኣን

"ለዳውድና ለሱለይማንም ዕውቀትን በእርግጥ ሰጠናቸው። አሉም፦ «ምስጋና ለአላህ ለእዚያ ከምእምናን ባሮቹ በብዙዎቹ ላይ ላበለጠን ይገባው።»"(27:15)

• ዳዊት በመፅሃፍ ቅዱስ የሰው ሚስት ቀምቶ ዝሙት ሰራ

"ዳዊትም መልእክተኞች ልኮ አስመጣት፤ ወደ እርሱም ገባች፥ ከርኩሰትዋም ነጽታ ነበርና ከእርስዋ ጋር ተኛ፤ ወደ ቤትዋም ተመለሰች።"(2ኛ ሳሙኤል 11:4)

"የእግዚአብሔር ባህሪ በመፅሀፍ ቅዱስ"

• ክርስትያን ወገኖች "አምላክ" ብለው እሚያመልኩት "እግዚአብሔር" ባህሪው ምን እንደሚመስል እንመልከት።

1•ምላጭ እሚከራይ

" በዚያም ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራየው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጕር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላል።"(ትንቢተ ኢሳያስ 7:20)

2•በፉጨት ተጣሪ

"በዚያም ቀን እንዲህ ይሆናል እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ዳርቻ ያለውን ዝምብ በአሦርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል(ትንቢተ ኢሳይያስ 7:18)

3•እሚጮህ

"እግዚአብሔር እንደ ኃያል ይወጣል እንደ ሰልፈኛም ቅንዓትን ያስነሣል ይጮኻል ድምፁንም ያሰማል

በጠላቶቹም ላይ ይበረታል”(ትንቢተ ኢሳይያስ 42:13)

4•እንደ ኣንበሳ እሚያገሳ

"እግዚአብሔርን ይከተላሉ፥ እርሱም እንደ አንበሳ ያገሣል ባገሣም ጊዜ ልጆች እየተንቀጠቀጡ ከምዕራብ ይመጣሉ:”(ትንቢተ ሆሴዕ 11:10)

5•ከፈጠረ በኃላ የሚያርፍና የሚተነፍስ

"እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በስድስት ቀን ስለ ፈጠረ፥ በሰባተኛውም ቀን ከሥራው ስላረፈና ስለ ተነፈሰ”(ኦሪት ዘጸአት 31:17)

6•የሚፀፀት

"እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ”(ኦሪት ዘፍጥረት 6:6)

7•በፈጠረው ፍጡር የሚሸነፍ

"አለውም፦ ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔር ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና”(ኦሪት ዘፍጥረት 32:28)

8•በእንቅልፋሞችና በሰካራሞች እሚመሰል

"እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፥ የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው”(መዝሙረ ዳዊት 78:65)

9•የስህተትን ኣሰራር የሚልክ

"እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል”(2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 2:12)

10•ኣታላይ

"አቤቱ፥ አታለልኸኝ እኔም ተታለልሁ፥ ከእኔም በረታህ አሸነፍህም ቀኑን ሁሉ መሳቂያ ሆኛለሁ፥ ሁሉም ያላግጡብኛል”(ትንቢተ ኤርምያስ 20:7)

11•ሰውን በማጥፋትና ሰውን በማፍረስ የሚደሰት

" እግዚአብሔር ሲያጠፋችሁ ሲያፈርሳችሁም ደስ ይለዋል"(ኦሪት ዘዳግም 28:63)

ሰዎን በማጥፋትና ሰውን በማፍረስ የሚደሰት አካል እንዴት ሆኖ አምላክ ሊሆን ይችላል?

12•በመጥፎ ነገር የሚያዝ

" ለጥፋት ለቀረበው ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት፥ ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት7 ይጠጣ ድህነቱንም ይርሳ፥ ጕስቍልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ"(መፅሃፈ ምሳሌ 31:6)

ፈጣሪ ሰዎች ከአስካሪ መጠጥ እንዲርቁ ነው እሚያዘው ወይስ "ብርቱ መጠጥ" ጠጥተው እንዲሰክሩ?

13•በዝሙት የሚያዝ

" እግዚአብሔር መጀመሪያ በሆሴዕ በተናገረ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሆሴዕን፦ ምድሪቱ ከእግዚአብሔር ርቃ ታላቅ ግልሙትና ታደርጋለችና ሂድ ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ አለው"
(ትንቢተ ሆሴእ 1:2)

ፈጣሪ ሰዎች ከዝሙት እንዲርቁ ነው እሚያዘው ወይስ "ሂድና ጋለሞታን ሴትና የግልሙትናን ልጆች ለአንተ ውሰድ"?

14•ለጨቅላ ህፃናት ርኅራሄ የሌለው ጨካኝ

"ሽማግሌውንና ጐበዙን ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ "
(ትንቢተ ህዝቂኤል 9:6)

ጨቅላ ህፃናትና ሽማግሌዎች እንዲገደሉ እሚያዝ አካል እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል?

15•ከተማና ግንብ ለማየት ከሰማይ ወደ ምድር የሚወርድ

“እግዚአብሔርም የአዳም ልጆች የሠሩትን ከተማና ግንብ ለማየት ወረደ”(ኦሪት ዘፍጥረት 11:5)

የተሰራው ግንብ ለማየት የግድ ወርዶ ማየት አለበት?ባለበት ሆኖ የተሰራው ግንብ ማየት አይችልም?

16•ልጅና ሚስት ያለው

“እስራኤል የበኩር ልጄ ነው”(ኦሪት ዘጸአት 4:23)

“ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፥ ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው”(ትንቢተ ኢሳይያስ 54:5)

ፈጣሪ ልጅና ሚስት ምን ይሰራለታል?

17•ኣንዱ በሰራው ሃጢኣት እስከ 10 ትውልድ ድረስ ሃጢኣተኛ እሚያደርግ

“ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ እስከ አሥር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ” (ኦሪት ዘዳግም 23:2)

ሁለት ሰዎች በሰሩት ኃጢአት እስከ አስር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሄር ጉባኤ እንዳይገቡ መከልከል ከፈጣሪ ፍትሃዊነት ጋር እንዴት ይታያል?

18•ነቢያትን አታላይ

“እግዚአብሔር በእነዚህ በነቢያትህ ሁሉ አፍ ሐሰተኛ መንፈስ አድርጎአል እግዚአብሔርም በላይህ ክፉ ተናግሮብሃል”(መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 22:23)

“ነቢዩም ቢታለል ቃልንም ቢናገር፥ ያንን ነቢይ ያታለልሁ እኔ እግዚአብሔር ነኝ”(ትንቢተ ሕዝቅኤል 14:9)

ለሰዎች ሞዴል አርአያ ሆነው እንዲያስተምሩ የላካቸው ነቢያት ማታለልና በነሱ ላይ ሐሰተኛ ማንፈስ ማድረግ ለምን?

19• ለራሱም ብርሃን ያጣ

“ሰሎሞንም። እግዚአብሔር፦ በጨለማ ውስጥ እኖራለሁ ብሎአል”(መጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 6:1)

“የእግዚአብሔርን ቀን ለምትፈልጉ ወዮላችሁ! የእግዚአብሔርን ቀን ለምን ትፈልጋላችሁ? ጨለማ ነው እንጂ ብርሃን አይደለም”(ትንቢተ አሞጽ 5:18)

እግዚአብሄር በጨለማ ውስጥ መኖር ለምን አስፈለገው?
ለራሱ ብርሃን ያላገኘን አካል ለኛ እንዴት ብርሃን ሊለግሰን ይችላል?

20• የሚተኛ

“አቤቱ፥ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ? ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን”(መዝሙረ ዳዊት 44:23)

እግዚአብሄር እውነተኛ አምላክ ከሆነ,መተኛት ለምን አስፈለገው?
ተኝቶ በፍጡራን እሚቀሰቀስ አካል እንዴት ሆኖ አምላክ ሊሆን ይችላል?
አምላክ በተኛበት ሰአት ፍጥረተ አለሙ በማን ቁጥጥር ስር ነበር?

21• ጫማ ምን ይሰራለታል?

"እንዲህም አለኝ። የሰው ልጅ ሆይ፥ በእስራኤል ልጆች መካከል ለዘላለም የምቀመጥበት የዙፋኔ ስፍራና የእግሬ ጫማ መረገጫ ይህ ነው።"(ትንቢተ ሕዝቅኤል 43:7)
ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ እግዚአብሄር ጫማ እንዳለው ይናገራል።
እግዚአብሄር እውነተኛ አምላክ ከሆነ,ለአምላክ የሚገባው ጫማ ምን አይነት ጫማ ነው?ደግሞስ ጫማ ምን ይሰራለታል?

"የሴቶች መብት በክርስትና"

ለሴቶች መብት ትልቅ ክብር,ለሴቶች መብት ትልቅ ደረጃ የሰጠ ብቸኛው መለኮታዊ ሃይማኖት "ኢስላም" ብቻ ነው።

• የሴቶች መብት በክርስትና ምን እንደሚመስል እንመልከት።

መፅሀፍ ቅዱስ ለሴቶች መብት ምንም ቦታ ያልሰጠ,ክብራቸውን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት መፅሀፍ ነው። የሴቶች መብት በመፅሀፍ ቅዱስ ምን ያህል የወረደ እንደሆነ በማስረጃ እንመልከት:

1.ከደረቅ ሴት የምድር ኣውሬ ይሻላል

“ከደረቅ ሴት ጋር ከምትኖር
ከምድር አውሪዎች ከ አንበሳዎች
ጋር መኖር ይሸላል”።(መጽሐፈ
ሲራክ 25:16)

2. ከሴት ቸርነት የወንድ ንፉግነት ይሻላል

“ከሴት ቸርነት የወንድ ንፉግነት
ይሸላል።ውሸማዋንና ባሏን
የምታቃና ሴት አፍረት ናት “።
(መጽሐፈ ሲራክ 42:14)

3. ኃጢኣት ሁሉ ከሴቶች ይገኛል

“ከልብስ ብል ይገኛል፤ኃጢያትም ሁሉ
ከሴቶች ይገኛል” (መጽሐፈ ሲራክ
42:13-14)

4. ሴት ሚስጥር ኣባካኝ

“ሚስጢርህን እንዳታወጣብህ ለሴት
ልብህን አትስጣት” (መጽሐፈ ሲራክ 9:5) “

5. የልብህን ሚስጥር ለሴት ኣታውጣላት

"በቤትህ አጠገብ ለውሀ መፍሰሻ አታበጅላት
ለሴት የልብህን ሚስጢር
አታውጣላት” (መጽሐፈሲራክ25:24)

6.ሚስትህንም ስለምትነግራት ቃል ተጠንቀቅ

”በእቅፍክ ለምትተኛዋ እንካ ስለ
ምትነግራት ቃል
ተጠንቀቅ”(ሚኪያስ7:5)

7•ከጠበኛ ሴት ማን ይሻላል?

"ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ቤት ከመቀመጥ በውጪ በቤት ማዕዘን ላይ መቀመጥ ይሻላል”(መጽሐፈ ምሳሌ 21:9)

8•ጠበኛ ሴት ከማን ጋር አንድ?

"በዝናብ ቀን የሚያንጠባጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው"(መጽሐፈ ምሳሌ 27:15)

9• ጠበኛ ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ

"ሰነፍ ልጅ ለአባቱ ኀዘን ነው፥ ጠበኛም ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት"(መጽሐፈ ምሳሌ 19:13)

10•የተጠላች ሴት ባል ካገኘች ምድር ትንቀጠቀጣለች

"በሦስት ነገር ምድር ትናወጣለች፥ አራተኛውንም ትሸከም ዘንድ አይቻላትም።
ባሪያ በነገሠ ጊዜ ሰነፍም እንጀራ በጠገበ ጊዜ፥
የተጠላች ሴት ባል ባገኘች ጊዜ፥ ሴት ባሪያም እመቤቷን በወረሰች ጊዜ።"(መጽሐፈ ምሳሌ 30:21-23)

11•የውርስ መብት የላትም

"ለእስራኤልም ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው። ሰው ቢሞት ወንድ ልጅም ባይኖረው፥ ርስቱ ለሴት ልጁ ይለፍሴት ልጅም ባትኖረው ርስቱን ለወንድሞቹ ስጡ
ወንድሞችም ባይኖሩት ርስቱን ለአባቱ ወንድሞች ስጡ
የአባቱም ወንድሞች ባይኖሩት ከወገኑ ለቀረበ ዘመድ ርስቱን ስጡ እርሱም ይውረሰው እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘ ለእስራኤል ልጆች ሥርዓትና ፍርድ ይሁን።"(ኦሪት ዘኍልቊ 27:8-11)

12•በ50 ብር ሴት ልጅ መድፈር

"ማናቸውም ሰው ድንግልና ያላትን ያልታጨች ልጃገረድ ቢያገኝ፥ ወስዶም ቢደርስባት፥ ቢያገኙትም፥
ያ የደረሰባት ሰው አምሳ የብር ሰቅል ለብላቴናይቱ አባት ይስጥ አስነውሮአታልና ሚስት ትሁነው በዕድሜውም ዘመን ሁሉ ሊፈታት አይገባውም።"(ኦሪት ዘዳግም 22:28-29)

13•እጇን ትቆረጥ

"ሁለት ሰዎች እርስ በርሳቸው ቢጣሉ፥ የአንደኛውም ሚስት ባልዋን ከሚመታው ሰው እጅ ታድነው ዘንድ ብትቀርብ፥ እጅዋንም ዘርግታ ብልቱን ብትይዝ፥
እጅዋን ቍረጥ፥ ዓይንህም አትራራላት።"(ኦሪት ዘዳግም 25:11-12)

14•ድንግል ያልሆነች ትገደል

"ነገሩ ግን እውነት ቢሆን፥ በብላቴናይቱም ድንግልናዋ ባይገኝ፥
ብላቴናይቱን ወደ አባትዋ ቤት ደጅ ያውጡአት፥ በእስራኤልም ዘንድ የማይገባውን ነገር አድርጋለችና፥ በአባትዋም ቤት አመንዝራለችና የከተማዋ ሰዎች እስክትሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩአት እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ ታስወግዳለህ።"(ኦሪት ዘዳግም 22:20-21)

15•የወር ኣበባ ያየች ሴት እርኩስ ነች

"ሴት ፈሳሽ ነገር ቢኖርባት በሥጋዋም ያለው ፈሳሽ ነገር ደም ቢሆን፥ በመርገምዋ ሰባት ቀን ትቀመጣለች የሚነካትም ሁሉ እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።
መርገምም ስትሆን የምትተኛበት ነገር ሁሉ ርኩስ ነው የምትቀመጥበትም ነገር ሁሉ ርኩስ ነው።
መኝታዋንም የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ድረስ ርኩስ ነው።
የምትቀመጥበትንም ነገር ሁሉ የሚነካ ሁሉ ልብሱን ያጥባል፥ በውኃም ይታጠባል፥ እስከ ማታም ርኩስ ነው።
በመኝታዋም ላይ ወይም በምትቀመጥበት ነገር ላይ ቢሆን ሲነካው እስከ ማታ ድረስ ርኩስ ነው።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 15:19-23)

16•ጋብቻ ያለ ፍላጎት

"ወንድማማቾች በአንድነት ቢቀመጡ፥ አንዱም ልጅ ሳይኖረው ቢሞት፥ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ ነገር ግን የባልዋ ወንድም ወደ እርስዋ ገብቶ እርስዋን ያግባ፥ ከእርስዋም ጋር ይኑር"(ኦሪት ዘዳግም 25:5)

17• ጭንቋ የበዛ

"ለሴቲቱም አለ፦ በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ በጭንቅ ትወልጃለሽ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፥ እርሱም ገዥሽ ይሆናል"(ኦሪት ዘፍጥረት 3:16)

18• በእሳት ትቃጠል

"የካህንም ልጅ ራስዋን በግልሙትና ብታረክስ አባትዋን ታረክሰዋለች በእሳት ትቃጠል"(ኦሪት ዘሌዋውያን 21:9)

19•የመናገር መብት የላትም

"ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና" (1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 14:34)

20•የማስተማር መብት የላትም

"ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም"(1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:12)

21•የተታለለች ሴቲቱ ነች

"የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ በመተላለፍ ወደቀች"(1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 2:14)

22•የተፈታች ሴት ማግባት ኣይፈቅድላትም

"ሚስትም ከባልዋ አትለያይ፥ ብትለያይ ግን ሳታገባ ትኑር"(1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 7:10)

23•ሚስት እንደ ባሪያ

"ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ”(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 5:22)

24• ሴት ደካማ ፍጥረት

"እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ ፍጥረት ስለ ሆኑ ከሚስቶቻችሁ ጋር በማስተዋል አብራችሁ ኑሩ"(1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3:7)

"ግድያ,ሰውን በእሳት ማቃጠልና ሰይፍ በመፅሀፍ ቅዱስ"

የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች ብዙውን ጊዜ,እስልምና የተስፋፋው በግድያ ነው,ቅዱስ ቁርአን ክርስትያን የገደለ ገነት ይገባል ይላል እያሉ ማስረጃ አልባ ክስ ይመሰርታሉ,ለዚህ ማስረጃ አልባ ክስ ማስረጃ ያለው በቂ ምላሽ ስለሚያስፈልገው,መልሱን በማስረጃ እንመልከት።

• በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ሰው የፈለገውን እምነት መከተል ይችላል።

እውነተኛው አምላካችን ኣላህ በሃይማኖት ማስገደድ እንደሌለ በተከበረው ቁርአኑ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

"በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ። በጣዖትም የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ። አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው።"(2:256)

«እውነቱም ከጌታችሁ ነው። የሻም ሰው ይመን፤ የሻም ሰው ይካድ» በላቸው።"(18:29)

•አምላካችን ኣላህ በሌላ የቁርአን አንቀፅ ምንም አይነት ብክለት ያላስፋፋች ነፍስ ማጥፋት ትልቅ ወንጀል እንደሆነ ሲነግረን እንዲህ ይለናል:

ነፍስን የገደለ ሰው ሰዎቹን ሁሉ እንደገደለ ነው፤ ሕያው ያደረጋትም ሰው ሰዎቹን ሁሉ ሕያው እንዳደረገ ነው።"(5:32)

ያቺንም አላህ ያወገዛትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ።"(17:33)

የቅዱስ ቁርአንን መልእክት በዚህ መልኩ ካየን,አሁን ደግሞ መፅሀፍ ቅዱስ ግድያን በተመለከተ ምን እንደሚል እንመልከት:

"የራሷ አሮባት የሰው ታማስላለች"

ግደሉ,እረዱ,አቃጥሉ እያለ እሚያዝ መፅሀፍ,የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች መፅሀፍ እንደሆነ ልብ ልትሉት ይገባል።

ግደሉ,እረዱ,አቃጥሉ የሚሉ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅሶች በርካታ ናቸው,ለናሙና ያክል "70" ጥቅሶችን እንመልከት:

1• "ሰው ሰውን ቢመታ ቢሞትም፥ እርሱ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 21:12)

2• "አባቱን ወይም እናቱን የሚመታ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 21:15)

3• "ሰውን ሰርቆ ቢሸጥ፥ ወይም በእጁ ቢገኝ፥ እርሱ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 21:16)

4• "አባቱን ወይም እናቱን የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 21:17)

5• "በሬው ግን አስቀድሞ ተዋጊ ቢሆን፥ ሰዎችም ለባለቤቱ ቢመሰክሩለት ባይጠብቀውም፥ ወንድንም ወይም ሴትን ቢገድል፥ በሬው ይወገር፥ ባለቤቱ ደግሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 21:29)

6• "ከእንስሳ ጋር የሚረክስ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 22:19)

7• "ስለዚህ ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ፤ የሚያረክሰውም ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል፥ ሥራንም በእርሱ የሠራ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘጸአት 31:14)

8• "ስድስት ቀን ሥራን ሥራ፤ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ የዕረፍት ሰንበት ነው፤ በሰንበት ቀን የሚሠራ ሁሉ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 31:15)

9• "ስድስት ቀን ሥራ ይደረጋል፥ ሰባተኛው ቀን ግን ለእግዚአብሔር የዕረፍት ሰንበት የተቀደሰ ቀን ይሆንላችኋል፤ የሚሠራበትም ሁሉ ይገደል።"(ኦሪት ዘጸአት 35:2)

10• "ደግሞ የእስራኤልን ልጆች እንዲህ በላቸው፦ ከእስራኤል ልጆች ወይም በእስራኤል ዘንድ ከሚቀመጡ እንግዶች ማናቸውም ሰው ዘሩን ለሞሎክ ቢሰጥ ፈጽሞ ይገደል፤ የአገሩ ሕዝብ በድንጋይ ይውገረው።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 20:2)

11• "ማናቸውም ሰው አባቱን ወይም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል፥ አባቱንና እናቱን ሰድቦአልና ደሙ በራሱ ላይ ነው።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 20:9)

12• "ማናቸውም ሰው ከእንስሳ ጋር ቢገናኝ ፈጽሞ ይገደል፤ እንስሳይቱንም ግደሉአት።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 20:15)

13• "የእግዚአብሔርንም ስም የሚሰድብ ፈጽሞ ይገደል፤ ማኅበሩም ሁሉ ይውገሩት፤ መጻተኛ ወይም የአገር ልጅ ቢሆን፥ የእግዚአብሔርን ስም በሰደበ ጊዜ ይገደል።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 24:16)

14• "ሰውንም እስኪሞት ድረስ የሚመታ ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘሌወሰውያን 24:17)

15• "እንስሳውንም የሚገድል ካሣ ይተካ፤ ሰውንም የሚገድል ይገደል"(ኦሪት ዘሌዋውያን 24:21)

16• "ማደሪያውም ሲነሣ ሌዋውያን ይንቀሉት፤ ማደሪያውም በሰፈረ ጊዜ ሌዋውያን ይትከሉት፤ ሌላ ሰው

ግን ቢቀርብ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 1:51)

17• "አሮንንና ልጆቹን አቁማቸው፥ ክህነታቸውንም ይጠብቁ፤ ሌላ ሰውም ቢቀርብ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 3:10)

18• "በማደሪያውም ፊት በምሥራቅ በኩል በመገናኛው ድንኳን ፊት በስተ ፀሐይ መውጫ የሚሰፍሩት ሙሴና አሮን ልጆቹም ይሆናሉ፥ መቅደሱንም ለእስራኤል ልጆች ይጠብቃሉ፤ ልዩም ሰው ቢቀርብ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 3:38)

19• "እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ሰውየው ፈጽሞ ይገደል፤ ከሰፈሩ ውጭ ማኅበሩ ሁሉ በድንጋይ ይውገሩት አለው።"(ኦሪት ዘኁልቁ 15:35)

20• "አንተም ከአንተም ጋር ልጆችህ ለመሠዊያው ሥራ የሚሆነውን ሁሉ፥ በመጋረጃውም ውስጥ የሚሆነውን ታደርጉ ዘንድ ክህነታችሁን ጠብቁ፥ አገልግሉም፤ ክህነቱን ለስጦታ አገልግሎት ሰጥቼአችኋለሁ ሌላም ሰው ቢቀርብ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 18:7)

21• "በብረት መሣርያ እስኪሞት ድረስ ቢመታው ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 35:16)

22• "ሰውም በሚሞትበት በእጁ ባለው ድንጋይ ቢመታው የተመታውም ቢሞት፥ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 35:17)

23• "ሰውም በሚሞትበት በእጁ ባለው በእንጨት መሣርያ ቢመታው የተመታውም ቢሞት፥ እርሱ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ነፍሰ ገዳዩም ፈጽሞ ይገደል።"(ኦሪት ዘኁልቁ 35:18)

24• "ወይም በጥላቻ እስኪሞት ድረስ በእጁ ቢመታው፥ የመታው ፈጽሞ ይገደል፤ ነፍሰ ገዳይ ነው፤ ደም ተበቃዩ ባገኘው ጊዜ ነፍሰ ገዳዩን ይግደለው።"(ኦሪት ዘኁልቁ 35:21)

25• "ሞት የተፈረደበትን ነፍሰ ገዳዩንም ለማዳን የነፍስ ዋጋ አትቀበሉ፤ እርሱ ፈጽሞ ይገደል"(ኦሪት ዘኁልቁ 35:31)

26• "አምላክህ እግዚአብሔር ትሄድባት ዘንድ ካዘዘህ መንገድ ሊያወጣህ፥ ከግብፅ ምድር ካወጣችሁ ከባርነትም ቤት ካዳናችሁ ከአምላካችሁ ከእግዚአብሔር ሊያስታችሁ ተናግሮአልና ያ ነቢይ ወይም ያ ሕልም አላሚ ይገደል፤"(ኦሪት ዘዳግም 13:5)

27• "በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች አፍ ሞት የሚገባው ይገደል"(ኦሪት ዘዳግም 17:6)

28• "ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ፥ እርሱ ይገደል።"(ኦሪት ዘዳግም 18:20)

29• "ነገር ግን ሰው የታጨችውን ልጃገረድ በሜዳ ቢያገኛት፥ በግድ አሸንፎም ቢደርስባት፥ ያ የደረሰባት ሰው ብቻውን ይገደል።"(ኦሪት ዘዳግም 22:25)

30• "አባቶች ስለ ልጆች አይገደሉ፥ ልጆችም ስለ አባቶች አይገደሉ፤ ነገር ግን ሁሉ እያንዳንዱ በኃጢአቱ ይገደል።"(ኦሪት ዘዳግም 24:16)

31• "በትእዛዝህ የሚያምፅ ሁሉ የምታዝዘውንም ቃል ሁሉ የማይሰማ፥ እርሱ ይገደል"(መጽሐፈ ኢያሱ 1:18)

32• "ንጉሡንም በዙሪያው ክበቡት፥ የጦር ዕቃችሁም በእጃችሁ ይሁን፤ በሰልፋችሁ መካከል የሚገባ ይገደል፤"(2ኛ ነገሥት 11:8)

33• "የእስራኤልንም አምላክ እግዚአብሔርን የማይፈልግ፥ ታናሽ ወይም ታላቅ፥ ወንድ ወይም ሴት ቢሆን፥ ይገደል"(2ኛ ዜና 15:13)

34• "ሌዋውያንም የጦር መሣሪያቸውን በእጃቸው ይዘው ንጉሡን በዙሪያው ይክበቡት፤ ወደ ቤቱም የሚገባ ይገደል"(2ኛ ዜና 23:7)

35• "ሽማግሌውንና ጐበዙን ቄንጆይቱንም ሕፃናቶቹንና ሴቶቹን ፈጽማችሁ ግደሉ"(ትንቢተ ሕዝቅኤል 9:6)

36• "እናንተ የዕብራውያንን ሴቶች ስታዋልዱ፥ ለመውለድ እንደደረሱ ባያችሁ ጊዜ፥ ወንድ ቢሆን ግደሉት"(ኦሪት ዘጸአት 1:16)

37• "ሙሴም የእስራኤልን ዳኞች፦ እናንተ ሁሉ ብዔልፌጎርን የተከተሉትን ሰዎቻችሁን ግደሉ አላቸው።"(ኦሪት ዘኁልቁ 25:5)

38• "በፌጎር በመቅሠፍቱ ቀን ስለተገደለችው ስለ ምድያም አለቃ ልጅ ስለ እኅታቸው ስለ ከስቢ በፌጎር ምክንያት በሸነገሉአችሁ ሸንገላ አስጨንቀዋችኋልና ምድያማውያንን አስጨንቁአቸው ግደሉአቸውም።"(ኦሪት ዘኁልቁ 25:17_18)

39• "አሁን እንግዲህ ከልጆቹ ወንዱን ሁሉ ግደሉ፥ ወንድንም በመኝታ የሚያውቁትን ሴቶች ሁሉ ግደሉ።"(ኦሪት ዘኁልቁ 31:17)

40• "እናንተ ግን አትዘግዩ፥ ጠላቶቻችሁንም አባርሩአቸው፥ በኋላም ያሉትን ግደሉ፤ አምላካችሁም እግዚአብሔር በእጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋልና ወደ ከተሞቻቸው እንዳይገቡ ከልክሉአቸው አለ።"(መጽሐፈ ኢያሱ 10:19)

41• "ማኅበሩም ወደዚያ አሥራ ሁለት ሺህ ኃያላን ሰዎች ሰድደው፦ ሂዱ በኢያቢስ ገለዓድም ያሉትን ሰዎች ከሴቶችና ከሕፃናት ጋር በሰይፍ ስለት ግደሉ።"(መጽሐፈ መሳፍንት 21:10)

42• "ንጉሡም በዙሪያው የቆሙትን እግረኞች፦ የእግዚአብሔር ካህናት እጅ ከዳዊት ጋር ነውና፥ ኩብለላውንም ሲያውቁ በጆሮዬ አልገለጡምና ዘራችሁ ግደሉአቸው አላቸው።"(1ኛ ሳሙኤል 22:17)

43• "አቤሴሎምም እንደ ንጉሥ ግብዣ ያለ ግብዣ አደረገ፤ አቤሴሎምም አገልጋዮቹን፦ አምኖን የወይን ጠጅ ጠጥቶ ልቡን ደስ ባለው ጊዜ እዩ። አምኖንን ግደሉ ባልኋችሁም ጊዜ ግደሉት፥ አትፍሩም ያዘዝኋችሁም እኔ ነኝና በርቱ ጽኑም ብሎ አዘዛቸው።"(2ኛ ሳሙኤል 13:28)

44• "የሚቃጠለውንም መሥዋዕት አቅርበው በፈጸሙ ጊዜ ኢዩ ዘበኞቹንና አለቆቹን፦ ግቡና ግደሉአቸው አንድም አይውጣ አላቸው። በሰይፍም ስለት ገደሉአቸው ዘበኞችና አለቆችም ወደ ውጭ ጣሉአቸው፥ ወደ በኣልም ቤት ከተማ ሄዱ።"(2ኛ ነገሥት 10:25)

45• "እኔም እየሰማሁ ለሌሎቹ፦ እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ መካከል እለፉ ግደሉም፤ ዓይናችሁ አይራራ አትዘኑም"(ትንቢተ ሕዝቅኤል 9:5)

46• "በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።"(የማቴዎስ ወንጌል 10:34)

47• "ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው በፊቴም እረዱአቸው"(የሉቃስ ወንጌል 19:27)

48• "እርሱም። አሁን ግን ኮረጆ ያለው ከእርሱ ጋር ይውሰድ፥ ከረጢትም ያለው እንዲሁ፤ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ።"(የሉቃስ ወንጌል 22:36)

49• "የካህንም ልጅ ራስዋን በግልሙትና ብታረክስ አባትዋን ታረክሰዋለች በእሳት ትቃጠል።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 21:9)

50• "ማናቸውም ሰው እናቲቱንና ልጂቱን ቢያገባ ርኩሰት ነው በመካከላችሁ ኃጢአት እንዳይሆን እርሱና እነርሱ በእሳት ይቃጠሉ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 20:14)

51• "እንዲህም ሆነ ከሦስት ወር በኋላ ለይሁዳ። ምራትህ ትዕማር ሴሰነች ደግሞም በዝሙት እነሆ ፀነሰች ብለው ነገሩት። ይሁዳም። አውጡአትና በእሳት ትቃጠል አለ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 38:24)

52• "እርም የሆነውም ነገር የተገኘበት ሰው የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አፍርሶአልና፥ በእስራኤልም ዘንድ በደል አድርጎአልና እርሱና ያለው ሁሉ በእሳት ይቃጠላሉ።"(መጽሐፈ ኢያሱ 7:15)

53• "ኢያሱም። ለምን አስጨነቅኸን? እግዚአብሔር ዛሬ ያስጨንቅሃል አለው እስራኤልም ሁሉ በድንጋይ ወገሩት በእሳትም አቃጠሉአቸው፥ በድንጋይም ወገሩአቸው።"(መጽሐፈ ኢያሱ 7:25)

54• "ሰባት ቀን ቂጣ እንጀራ ትበላላችሁ፤ በመጀመሪያም ቀን እርሾውን ከቤቶቻችሁ ታወጣላችሁ፤ ከመጀመሪያውም ቀን አንሥቶ እስከ ሰባተኛው ቀን እርሾ ያለበትን እንጀራ የሚበላ ነፍስ ከእስራኤል ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘጸአት 12:15)

55• "ሰባት ቀን በቤታችሁ እርሾ አይገኝ፤ እርሾ ያለበትንም እንጀራ የሚበላ ነፍስ፥ ከመጻተኛው ጀምሮ እስከ አገር ልጁ ድረስ፥ ከእስራኤል ማኅበር ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘጸአት 12:19)

56• "ከእግዚአብሔር በቀር ለአንዳች አምላክ የሚሠዋ ፈጽሞ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘጸአት 22:20)

57• "ስለዚህ ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ፤ የሚያረክሰውም ሰው ሁሉ ፈጽሞ ይገደል፥ ሥራንም በእርሱ የሠራ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘጸአት 31:14)

58• "ሰውም የረከሰ ቢሆን፥ ለእግዚአብሔርም ከሆነው ከደኅንነት መሥዋዕት ሥጋ ቢበላ፥ ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 7:20)

59• "ማናቸውንም ርኩስ ነገር ቢነካ፥ የሰውን ወይም የረከሰን እንስሳ ወይም ሌላውን የተጠላ ርኩስን ቢነካ፥ ለእግዚአብሔርም ከሆነው ከደኅንነት መሥዋዕት ሥጋ ቢበላ፥ ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 7:21)

60• "ደም የሚበላ ሰው ሁሉ ያ ሰው ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 7:27)

61• "በእግዚአብሔር ማደሪያ ፊት ለእግዚአብሔር ቍርባን ያቀርብ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባያመጣው፥ ደሙ በዚያ ሰው ላይ ይቈጠርበታል፤ ደም አፍስሶአል፤ ያም ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 17:4)

62• "ለእግዚአብሔር ይሠዋ ዘንድ ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ ባያመጣው፥ ያ ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 17:9)

63• "የሥጋ ሁሉ ሕይወትና ደሙ አንድ ነውና ስለዚህ ለእስራኤል ልጆች፦ የሥጋ ሁሉ ሕይወት ደሙ ነውና የሥጋውን ሁሉ ደም አትብሉ፤ የሚበላውም ሁሉ ተለይቶ ይጥፋ አልኋቸው።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 17:14)

64• "የበላውም ለእግዚአብሔር የተቀደሰውን ነገር አርክሶአልና ኃጢአቱን ይሸከማል፤ ያም ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 19:8)

65• "እንዲህ በላቸው፦ ማናቸውም ሰው ከዘራችሁ በትውልዳችሁ ርኩሰት እያለበት የእስራኤል ልጆች ለእግዚአብሔር ወደሚቀድሱት ወደ ቅዱስ ነገር ቢቀርብ፥ ያ ሰው ከፊቴ ተለይቶ ይጥፋ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 22:3)

66• "በዚያም ቀን የማይዋረድ ሰው ሁሉ ከሕዝቡ ተለይቶ ይጥፋ።"(ኦሪት ዘሌዋውያን 23:29)

67• "የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ናቀ፥ ትእዛዙንም ስለ ሰበረ፥ ያ ሰው ፈጽሞ ይጥፋ፤ ኃጢአቱ በራሱ ላይ ነው።"(ኦሪት ዘኍልቁ 15:31)

68• "በዚያን ጊዜም ኢያሱ፦ ይህችን ከተማ ኢያሪኮን ለመሥራት የሚነሣ ሰው በእግዚአብሔር ፊት ርጉም ይሁን፤ መሠረትዋን ሲጀምር በኵር ልጁ ይጥፋ፥ በርዋንም ሲያቆም ታናሹ ልጁ ይጥፋ ብሎ ማለ።"(መጽሐፈ ኢያሱ 6:26)

69• "የእናትህ ልጅ ወንድምህ ወይም ወንድ ልጅህ ወይም ሴት ልጅህ ወይም በብብትህ ያለች ሚስትህ ወይም እንደ ነፍስህ ያለ ወዳጅህ በስውር። ና፥ ሄደን ከምድር ዳር ጀምሮ እስከ ምድር ዳር ድረስ ወደ አንተ የቀረቡት ከአንተም የራቁት አንተን ከብበውህ ያሉ አሕዛብ ከሚያመልኩአቸው አማልክት፥ አንተም አባቶችህም የማታውቋቸውን ሌሎች አማልክት እናምልክ ብሎ ቢያስትህ፥ እሺ አትበለው፥አትስማውም፤ ዓይንህም አይራራለት፥ እትማረውም፥ አትሸሽገውም፤ነገር ግን ፈጽመህ ግደለው፤ እርሱን ለመግደል በፊት የአንተ እጅ፥ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ትሁን"(ኦሪት ዘዳግም 13:6_9)

70• "ማናቸውም ሰው ቢኰራ፥ በዚያም አምላክህን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቆመውን ካህኑን ወይም ፈራጁን ለመስማት ባይወድድ፥ ያ ሰው ይሙት፥ ከእስራኤልም ዘንድ ክፋትን አስወግድ"(ኦሪት ዘዳግም 17:12)

ስለ ነብዩ ሙሐመድ(ሰላሉሁ ዐለይሂ ወሰለም) የተነገረ ትንቢት

የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች,የነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) እውነተኛ ነብይነት ለማስተባበልና ላለመቀበል,ነብዩ ሙሐመድ(ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እውነተኛ ነብይ ከሆኑ ስለሳቸው ነብይነት አስቀድሞ የተነገረ ትንቢት አሳዩን እያሉ ይጠይቃሉ።

አንድ ነብይ እውነተኛ የፈጣሪ ነብይ ነው ብለን አምነን ለመቀበል ስለዛ ነብይ አስቀድሞ ትንቢት መነገሩ ለነብይነቱ መስፈርት አይደለም።

ክርስትያን ወገኖች የፈጣሪ ነብያት ብለው የሚያምኑባቸው አብዛኞቹ ትንቢት አልተነገረላቸውም።

ለምሳሌ:

"አሁንም የሰውዬውን ሚስት መልስ ነቢይ ነውና፥ ስለ አንተም ይጸልያል፥ ትድናለህም። ባትመልሳት ግን አንተ እንድትሞት ለአንተ የሆነውም ሁሉ እንዲሞት በእርግጥ እወቅ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 20:7)

ይህ የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ አብርሃም ነብይ እንደሆነ ይናገራል።

የኛ ጥያቄ: ስለ አብርሃም ነብይነት አስቀድሞ የተነገረ ትንቢት ከመፅሀፍ ቅዱስ አሳዩን?

እኛ ሙስሊሞች እንደምናምነው ስለ ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) ነብይነት ትንቢትን ሳይናገር ያለፈ አንድ ነብይ የለም።

ለዚህ እምነታችን በቂ የሆነ ማስረጃ ከቅዱስ ቁርአንና ከመፅሀፍ ቅዱስ እናቀርባለን።

በቅዱስ ቁርአን ስለ ነብዩ ሙሐመድ(ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይነት የተነገሩ ትንቢቶች:

1• ሁሉም ነብያቶች ነብዩ ሙሐመድ(ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ነብይ ሆነው ሲላኩ በሂወት ቢያገኙዋቸው ነብይነታቸው አምነው እንደሚቀበሉ ቃል ገብቷል።

"አላህ የነቢያትን ቃል ኪዳን፣ ከመጽሐፍና ከጥበብ ሰጥቻችሁ ከዚያም ከእናንተ ጋር ላለዉ (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ መልክተኛ ቢመጣላቸዉ፣ በርሱ በእርግጥ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል በያዘ ጊዜ (አስታዉስ)፤ አረጋገጣችሁን? በይሃችሁ ላይ ኪዳኔን ያዛችሁምን? አላቸዉ፤ አረጋገጥን አሉ እንግዲያስ መስክሩ፤ እኔም ከእናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ አላቸዉ"(3:81)

2• ነብዩላህ ኢብራሂምና ልጃቸው ኢስማዒል(ዐለይሁሙ ሰላም) ነብያችን ዐለይሂ ሰላት ወሰላም ነብይ ሆነው ከመላካቸው በፊት ያደረጉት ዱዓ

"«ጌታችን ሆይ! በውስጣቸውም ከነሱው የኾነን መልክተኛ በነርሱ ላይ አንቀጾችህን የሚያነብላቸውን

መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራቸውን (ከክህደት) የሚያጠራቸውንም ላክ፤ አንተ አሸናፊው ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና» (የሚሉም ሲኾኑ)"(2:129)

ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) በሐዲሳቸው ሲናገሩ "እኔ የአባቴ የኢብራሂም ዱዓ ነኝ(2:129),የወንድሜ የዒሳ ብስራት ነኝ(61:6)"

3•የነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) ባህሪ ምን እንደሚመስል በተውራት አስቀድሞ ተነግሯል።

"ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ)፤ በበጎ ስራ ያዛቸዋል፤ ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል፤ መልካም ነገሮችንም ለነርሱ ይፈቅድላቸዋል፤ መጥፎ ነገሮችም በርሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከነርሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በነሱ ላይ የነበርሩትን እንዛዝላዎች (ከባድ ሕግጋቶች) በርሱ ያመኑ ያከበሩትም የረዱትም ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ እነዚያ እነሱ የሚድኑ ናቸው።"(7:157)

ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) መፃፍም ሆነ ማንበብ አይችሉም ነበር።

"ከርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትጽፈው አልነበርክም፤ ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጉ ነበር።"(29:48)

4• ነብዩላህ ዒሳ(ዐለይሂ ሰላም) ስለሳቸው ነብይነት በኢንጅል አስቀድሞ ትንቢትን ተናግሯል።

"የመርየም ልጅ ዒሳም የ እስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ (አስታውስ)፤በግልጽ ታምራቶች በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ።
"(61:6)

ክርስትያኖችና አይሁዶች ልጆቻቸውን ጠንቅቀው እንደሚያውቋቸው ሁሉ,ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላምም) እውነተኛ የፈጣሪ ነብይ መሆናቸው ጠንቅቀው ያውቃሉ።

እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል። እነዚያ ከእነርሱ ውስጥ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩት እነርሱ አያምኑም።"(6:20)

ስለ ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) ነብይነት በመፅሀፍ ቅዱስ የተነገረ ትንቢት

1•

"ደግሞም መፅሓፉን ማንበብ ለማያውቅ ይህን ኣንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ማንበብ ኣላውቅም ይላቸዋል"(ትንቢተ ኢሳያስ 29:12)

ይህ ትንቢት ለነብያችን ዐ•ሰ•ወ የተነገረ ትንቢት ነው,እንዴት የሚል ጥያቄ ከተነሳ

— ነብያችን ዐ•ሰ•ወ መላኢካው ጅብሪል ለመጀመሪያ ጊዜ ከኣላህ ይዞላቸው የመጣው መልእክት ኢቅራእ(ኣንብብ) የሚል ነበር።

ነብያችን ዐ•ሰ•ወ ኢቅራእ(ኣንብብ) ሲባሉ,ማኣነ ቢቃሪእ(እኔ ማንበብ ኣላውቅም) ብለው መለሱ።

በሌላ የቁርኣን ኣየት

" ለነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብ ነብይ የሆነውን መልክተኛ የሚከተሉ ለሆኑት (በእርግጥ እጽፋታለሁ)"(7:157)

በዚህ የቁርኣን ኣየት ደግሞ "የማይፅፍና የማያነብ ነብይ" በማለት ባህሪያቸውን ነገረን።

በሌላ የቁርኣን ኣየት ደግሞ

"ከእርሱ በፊትም መፅሓፍን የምታነብ በቀኝህም የምትፅፈው ኣልነበርክም
ያን ጊዜ ኣጥፊዎቹ በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር"(29:48)

ከዚህ ኣንፃር ይህ ትንቢት ለነብያችን ዐ•ሰ•ወ የተነገረ ትንቢት ነው ብለን እናምናለን።

2•

"የምነግራችሁ ገና ብዙ ኣለኝ ነገር ግን ኣሁን ልትሸከሙት ኣትችሉም
ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ
ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኃል የሚሰማውን ሁሉ ይነግራችኃል እንጂ ከራሱ ኣይነግርምና የሚመጣውንም ይነግራችኃል"
(ዬሐንስ ወንጌል 16:12— 13)

ይህ ትንቢት ለነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) የተነገረ ትንቢት ነው,እንዴት ከተባለ
"የሚሰማውን ሁሉ ይነግራችኃል እንጂ ከራሱ ኣይነግርምና" ይላል

የነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) ባህሪ በቁርኣን ደግሞ

"ከልብ ወለድም ኣይናገረም እርሱ ንግግሩ የሚወረድለት ራእይ እንጂ ሌላ ኣይደለም"(53:3— 4)

ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) የተወረደላቸው ራእይን እንጂ ከራሳቸው(ከልብወለዳቸው) ኣልተናገሩም።

ከዚህ ኣንፃር ይህ ትንቢት ለነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) የተነገረ ትንቢት ነው ብለን እናምናለን።

3•

"ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነብይ ኣስነሳላቸዋለሁ ቃሌንም በኣፉ ኣደርጋለሁ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታሎ"(ኦሪት ዘዳግም 18:18)

ይህ ትንቢት ደግሞ ሰፋ ኣድርገን እንየው

— ከወንድሞቻቸው መካከል:

ሁላችንም እንደምናውቀው እስራኤላውያኖች የኢስሓቅ ዘር ሲሆኑ
ኣረቦች ደግሞ የእስማዔል ዘር ናቸው።
ኢስሓቅና እስማዔል ደግሞ ወንድማማቾች ናቸው።

ስለዚ ከወንድሞቻቸው መካከል ሲል የሚነሳው ነብይ ለእስራኤላውያን ወንድሞች ከሆኑት ከኣረቦች ነው።

—እንዳንተ ያለ ነብይ:
ያ የሚነሳው ነብይ ደግሞ ሙሴን የመሰለ ነብይ መሆን ኣለበት።

ሙሴና ነብዩ ሙሓመድ ዐ•ሰ•ወ ደግሞ በብዙ ነገር ይመሳሰላሉ:

1•የተፈጠሩት ከወንድና ከሴት ፆታዊ ግንኙነት ነው።
2•ነብይ ናቸው።
3•ኣግብተው ወልደዋል።
4•ተፈጥሮወኣዊውን ሞት ሞቷል።

—ቃሌንም በኣፉ ኣደርጋሎ
ነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) በመላኢካው ጅብሪል(ዐለይሂ ሰላም) ኣማካኝነት የጌታችን ቃል በኣፋቸው ተደርጎላቸው ሲያስተምሩ ነበር።

—በስሜም የሚናገረውን ቃል
እያንዳንዱ የቁርኣን ምእራፍ ምእራፍ 9 ሲቀር "በኣላህ ስም እጅግ በጣም ርኃሩኃ በጣም ኣዛኝ በሆነው" እያለ ነው የሚጀምረው።

ከዚህ ኣንፃር ይህ ትንቢት ለነብያችን(ዐለይሂ ሰላት ወሰላም) የተነገረ ትንቢት ነው ብለን እናምናለን።

ክርስትያን ወገኖች ይሄ ትንቢት ለኢየሱስ የተነገረ ትንቢት ነው ይሉናል,በእውቀት መነፅር እስቲ እንየው

ኢየሱስ ኣምላክ ነው ፈጣሪ ነው ብለው ያምናሉ,ነገሩ እንዲህ ከሆነ

—ከወንድሞቻቸው መካከል
እየሱስ ኣምላክ ከሆነ,የኣምላክ ወንድሞች እነማን ናቸው?ኣምላክ ወንድሞች ኣሉት ወይ?

—እንዳንተ ያለ ነብይ
የሚነሳው ነብይ ከእስራኤል ሊሆን ኣይችልም ለምን ከተባለ

"እግዚኣብሄርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ከዚህ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ ኣልተነሳም" (ኦሪት ዘዳግም 34:10)
ተብሎ ተፅፎዋልና።

ኣምላክ ብለው የሚያመልኩት ኢየሱስ ነብይ ከሆነ,ኣምላክ ነብይ በነበረበት ሰኣት ፍጥረተ ኣለሙ በማን ቁጥጥር ስር ነበር???

— ቃሌንም በኣፉ ኣደርጋሎ

ኢየሱስ ኣምላክ ከሆነ,ለኣምላክ ቃሉን በኣፉ የሚያደርግለት ማነው???

የዚህ ትንቢት ተናጋሪው ማነው????

ክርስትያን ወገኖች ማስረጃው በናንተ ላይ ተረገግጧል

እላንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! አብሳሪና አስፈራሪ አልመጣልንም እንዳትሉ ከመልክተኞች በመቋረጥ ጊዜ ላይ ሲኾን (ሕጋችንን) የሚያብራራ ሆኖ መልክተኛችን በእርግጥ መጣላችሁ። አብሳሪና አስፈራሪም በእርግጥ መጣላችሁ። አላህም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።"(5:19)

"ጳውሎስ ማነው"???

1•የኢየሱስ ሐዋሪያ ያልነበረ ሰው

"የአሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ስም ይህ ነው፤ መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን ወንድሙ እንድርያስም፥ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም ወንድሙ ዮሐንስም፥
ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥ ቶማስም ቀራጩ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ታዴዎስም የተባለው ልብድዮስ፥
ቀነናዊውም ስምዖን ደግሞም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።"(ማቴዎስ 10:2_4)

2•የኃጢኣተኞች ቁንጮ

"ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤"(1ኛ ጢሞቴዎስ 1:15)

3•ሞኝና ትምክህተኛ

"እንደዚህ ታምኜ ስመካ የምናገረው፥ በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም"(2ኛ ቆሮንጦስ 11:17)

4•የሰይጣን መልእክተኛ የተሰጠው

"ስለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎስመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው"(2ኛ ቆሮንጦስ 12:7)

5•ሕግን የሻረ

"ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች"(እብራውያን 7:18-19)

6•ዘረኛ

"እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤"(ገላትያ 2:15)

7•የሴቶች የመናገር መብት የተጋፋ ሰው

"ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና።” (1ኛ ቆሮንጦስ 14:34)

8•የሴቶች የማስተማር መብት የከለከለ ሰው

"ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም”(1ኛ ጢሞቴዎስ 2:12)

9•የግል ታሪኩን እንደ ፈጣሪ ቃል ለማስመሰል የሞከረ ሰው

"ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ”(2ኛ ጢሞቴዎስ 4:13)

10• ፈጣሪ የደነገገው ግርዛት ምንም አይጠቅምም ይለናል

"እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ። ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም።"(ገላትያ 5:2)

11•ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዮ ነበር ይለናል።

እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና።ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤"(ገላትያ 2:19_20)

12• በእንጨት የሚሰቀል የተረገመ ነው

"በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፤"(ገላትያ 3:13)

13• ሁሉም ምግብ የፈቀደ

"በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ ሳትመራመሩ ብሉ፤"(1ኛ ቆሮንጦስ 10:25)

14• እግዚአብሄር ሞኝነት አለበትን?

"ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ ይበረታልና።"(1ኛ ቆሮንጦስ 1:25)

15• ብዙ ተባዙ እሚለውን ትእዛዝ የተቃወመ ሰው

"ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።"(1ኛ ቆሮንጦስ 7:1)

16• ዘራፊ

"እናንተን ለማገልገል ደመወዝ እየተቀበልሁ ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት ዘረፍሁ።"(2ኛ ቆሮንጦስ 11:8)

17• ብሉይ ኪዳንን የሻረ

"አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ስለ ሞትን፥ ከሕግ ተፈትተናል፥ ስለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።"(ሮሜ 7:6)

18• ጎስቋላ

"እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ!"(ሮሜ 7:24)

19• የኃጢአት ባሪያ

"በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ እገዛለሁ።"(ሮሜ 7:25)

20• እግዚአብሄርን በውሸት ያላቀ

"በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ስለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል?"(ሮሜ 3:7)

21• መልካም እንዲመጣ ክፉ እናድርግ የሚል ሰው

"ስለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ አናደርግም?"(ሮሜ 3:8)

22• አስካሪ መጠጥን እሚያበረታታ

"ስለ ሆድህና ስለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ።"(1ኛ ጢሞቴዎስ 5:23)

23• ሰዎች ከሰይጣን ምን ሊማሩ ነው ለሰይጣን የሰጣቸው?

"ከእነዚያም፥ እንዳይሳደቡ ይማሩ ዘንድ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፥ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።"(1ኛ ጢሞቴዎስ 1:20)

"መልስ እንፈልጋለን የተረዳ ካለ"

1•ኢየሱስ ክርስቶስ በመፅሃፍ ቅዱስ በማያሻማና በማያጠራጥር ኣገላለፅ "እኔ ኢየሱስ ኣምላክ ነኝ ወይም ፈጣሪ ነኝ" ያለበት 1 ጥቅስ ከመፅሃፍ ቅዱስ ኣሳዩኝ?

2•እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ ለኣዳም "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ ተሰቅዬ ኣድናሃሎ" ብሎ ቃል እንደገባለት የሚናገር 1 ጥቅስ ከመፅሃፍ ቅዱስ ኣሳዩኝ?

3•መፅሃፋቸሁን "መፅሃፍ ቅዱስ" ብሎ የሰየመው ማነው?

4•መፅሃፍ ቅዱስ የሚለው ቃሉ ራሱ በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የት ይገኛል?

5•የሃይማኖታችሁ መጠሪያ "ክርስትና" ብሎ የሰየመው ማነው?

6•ክርስትና የሚል ቃል በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥ የት ይገኛል?

7•እኔ "ክርስትያን ነኝ" ወይም "ክርስትያን ሁኑ" ብሎ የሰበከ 1 የፈጣሪ ነብይ ኣሳየኝ?

8•እግዚኣብሄር በመፅሃፍ ቅዱስ "እኔ እግዚኣብሄር ኣንድም ሦስትም ነኝ" ያለበት 1 ጥቅስ ኣሳየኝ?

9•እግዚአብሄር በመፅሀፍ ቅዱስ አንድ ሚስት ብቻ አግቡ ወይም ከአንድ ሚስት በላይ አታግቡ ብሎ የተናገረበት 1 ጥቅስ አሳየን?

"ከ1 ሚስት በላይ ማግባት በመፅሀፍ ቅዱስ"

የክርስትና እምነት ተከታይ ወገኖች ቁርአን ከአንድ ሚስት በላይ ማግባት ለምን ፈቀደ እያሉ ከአንድ በላይ ማግባትን ይቃወማሉ።

ወገኖቻችን ይሄን ጥያቄ እሚያነሱት መፅሀፋቸውን በአግባቡ ባለመረዳታቸው ነው።
እግዚአብሄር በመፅሀፍ ቅዱስ "አንድ ሚስት ብቻ አግቡ ወይም ከአንድ ሚስት በላይ አታግቡ" ብሎ የተናገረበት አንድ ጥቅስ የለም።

እንደ መፅሀፍ ቅዱስ አስተምህሮት ብዙ ሰዎች,ከአንድ በላይ ሚስት እንደነበራቸው ይገልፃል።

ለምሳሌ:

1•ሰሎሞን 700 ሚስቶች

"ለእርሱም ወይዛዝር የሆኑ ሰባት መቶ ሚስቶች ሦስት መቶም ቁባቶች ነበሩት፤ ሚስቶቹም ልቡን አዘነበሉት።"(1ኛ ነገሥት 11:3)

2• ላሜሕ 2 ሚስቶች

"ላሜሕም ለራሱ ሁለት ሚስቶችን አገባ፤ የአንዲቱ ስም ዓዳ፥ የሁለተኛይቱ ስም ሴላ ነበረ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 4:19)

3• ጌዴዎን ብዙ ሚስቶች

"ለጌዴዎንም ብዙ ሚስቶች ነበሩትና ከወገቡ የወጡ ሰባ ልጆች ነበሩት።"(መፅሃፈ መሳፍንት 8:30)

4• አሸሑር 2 ሚስቶች

"ለቴቁሔም አባት ለአሸሑር ሔላና ነዕራ የተባሉ ሁለት ሚስቶች ነበሩት።"(1ኛ ዜና 4:5)

5• ኣብያ 14 ሚስቶች

"አብያም ጸና፥ አሥራ አራትም ሚስቶች አገባ፥ ሀያ ሁለትም ወንዶች ልጆችንና አሥራ ስድስት ሴቶች ልጆችን ወለደ።"(2ኛ ዜና 13:21)

6• ዮዳሄ 2 ሚስቶች

"ዮዳሄም ሁለት ሚስቶች አጋባው፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለደ"(2ኛ ዜና 24:3)

7• ሕልቃና 2 ሚስቶች

"ሁለትም ሚስቶች ነበሩት፤ የአንዲቱ ስም ሐና የሁለተኛይቱም ስም ፍናና ነበረ"(1ኛ ሳሙኤል 1:2)

8• ለ1 ሰው 2 ሚስቶች ቢኖሩት

"ለአንድ ሰው አንዲቱ የተወደደች አንዲቱም የተጠላች ሁለት ሚስቶች ቢኖሩት፥"(ኦሪት ዘዳግም 21:15)

በተለይ በዚህ ጥቅስ እራሱ እግዚአብሄር ሲናገር,ለአንድ ሰው አንዲቷ የተወደደች አንዷ የተጠላች ሁለት ሚስት ቢኖሩት በማለት,አንድ ሰው ከአንድ ሚስት በላይ እንደሚኖረው ይገልፃል።ዲቷ

ከአንድ ሚስት በላይ እማይፈቀድ ከሆነ,እዚህ ላይ እግዚአብሄር ለምን አልተቃወመም?

9• ዳዊት ብዙ ሚስቶች

"ዳዊትም በኢየሩሳሌም ሚስቶችን ጨምሮ ሌሎችን ወንዶችንና ሴቶችን ልጆች ወለደ።"(1ኛ ዜና 14:3)

10• ኣብራም 3 ሚስቶች

"የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው።"(ኦሪት ዘፍጠረት 16:3)

"አብርሃምም ደግሞ ስምዋ ኬጡራ የተባላች ሚስት አገባ።"(ኦሪት ዘፍጥረት 25:1)

ማጠቃለያ

ኢስላም እውነተኛውና ብቸኛው መለኮታዊ ሃይማኖት ነው።

አላህም ወደ ሰላም አገር(ጀነት) ይጠራል። የሚሻውንም ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል።"(10:25)
አላህም እውነቱን ይናገራል፤ እርሱም ትክክለኛዉን መንገድ ይመራል።"(33:4)

አላህ ዘንድ (የተወደደ) ሃይማኖት ኢስላም ብቻ ነዉ፣ "(3:19)
ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰዉ፣ ፈጽሞ ከርሱ ተቀባይ የለዉም፤ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎች ነዉ።"(3:85)
እላንተ ያመናችሁ ሆይ! አላህን ተገቢዉን መጠንቀቅ ተጠንቀቁት፤ እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጅ አትሙቱ።"(3:102)
እነዚያ የካዱት (በትንሣኤ ቀን) ሙስሊሞች በኾኑ ኖሩ በብዛት ይመኛሉ"(15:2)

ሙስሊም ላልሆኑት ወገኖች አላህ ሂዳያውን ይስጣቸው,ለኛም ፅናቱን ይስጠን,ሙስሊም አድርጎ እንደፈጠረን,ሙስሊም አድርጎ ያኑረን,ሙስሊም አድርጎም ይግደለን።

ጌታችን ሆይ! በኛ ላይ ትግእስትን አፍስስ፤ ሙስሊሞች ሆነን ግደለን"(7:126)